# መግቢያ

በሀገራችን መንግስታዊ ተቋማት አገልግሎቶችን የተሻሻለና ወቅታዊ ቀልጣፋና ፈጣን ለማድረግ ከወጡት የተለያዩ ፖሊሲዎችና መመሪያዎች መካከል በዋናነት መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/ እና ይህን ለማስፈጸም ተቀርጾ የቀረበው ሚዛናዊ ውጤት ተኮር ዕቅድ /BSC/ ዓይነተኛ የለውጥ መሣሪያ በመሆን በየመንግስት ተቋማቱ የለውጥ መሣሪያ በመሆን ለዜጎች ወይም ለሕብረተሰቡ የሚሰጠውን አገልግሎት ብቃትና ጥራት ያለው ሆኖ እንዲገኝ ፈጣን ፣ ቶሎ ምላሽ ሰጪ ግልጽና ተጠያቂነት ያለበት እንዲሆን በማስቻል ላይ ይገኛል፡፡

በመሆኑም በክልላችን መንግስት የተገኘውን ለውጥና መሻሻሎችን የበለጠ ለማስቀጠል እና የአገልግሎት አሰጣጣችን ግልጽና ተጠያቂነት ያለበት እንዲሆን በማሰብ አገልግሎት ሰጭ ተቋማትና አገልግሎት ተቀባይ ሕብረተሰብ ፈጣንና የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠትና ለማስገኘት ስታንደርዶችን መሠረት በማድረግ ይህን ስታንደርድ አዘጋጅቶ ተቋምና ባለድርሻ አካላት በጋራ በመሆን የሚያፀድቁትና ተግባራዊ የሚደረገው የዜጎች ቻርተር በክልሉ በሚገኙ ተቋማት እንዲዘጋጁ ተደርጓል፡፡

በዚሁ መሠረት በሀዋሣ ከተማ ፍ/ቤቶች በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሠረት  የተገልጋይ መብት ለማስጠበቅ፣ የተገልጋዩን አመኔታ እርካታና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ምን አይነት አገልግሎት በምን ያህል ፣ ጥራት ፣ ጊዜ ወጪ መፈጸም እንዳለባቸው ሁኔታዎችን ግልጽ ለማድረግ የተቀመጠ የአሰራር ስልት ባለመኖሩ  ክፍተቶችን የሚሞሉ ስታንደርዶችን በማዘጋጀት ለህብረተሰቡ  ቃል መግባት እንዲቻል ይህ የፍርድ ቤቶች የዜጎች ቻርተር ሰነድ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

## 1. የቻርተር ዓላማ

- ለተገልጋዮች ተአማንነት ያለው ፈጣን ፍትህ የማግኘት መብት ለማረጋገጥ
- ለተገልጋዮች ግልጽና ጥራት ያለውን አገልግሎት መስጠት
- የተገልጋዮችን አመኔታና እርካታ ለመፍጠርና ተጠቃሚነትን በየደረጃው ለማረጋገጥ
- ተጠያቂነትን በግልጽ ለማመልከት
- ተገልጋዮች ምን ዓይነት አገልግሎት ፣ በምን ያህል ጊዜ፣በምን ጥራት ደረጃ፣ በየትኛው ቦታ ማግኘት እንደሚገባቸው ለማሣወቅ፣
- ተገልጋዮች በፍ/ቤቶች አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የባለቤትነት ስሜት ተሰምቶአቸው አስተያየት ፣ ጥቆማና ግብአት የሚሆኑ የማሻሻያ ሀሣቦችን የሚሰጠበትን ሁኔታና ሥርዓት ለማመቻቸት
- ፍ/ቤቶችን ቀልጣፋ ውጤታማና ተደራሽ ለማድረግ
- ውጤታማና ተገማችነት ያለው አገልግሎት አሰጣጥ ለማረጋገጥ
- የሚመለከታቸው አካላትና ሕብረተሰቡ በፍትህ ሥርዓቱ ላይ ዘላቂነት ባለው ሁኔታ በመሣተፍ የጕላ ሚናቸውን እንዲጫወቱ ለማስቻል ነው፡፡

## 2. የተቋሙ ስምና አድራሻ

የሀዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የሚገኝበት በሀዋሣ ከተማ መናኸሪያ ክ/ከተማ ሚሊኒየም ቀበሌ ከቤተሰብ መምሪያ ወደ አውቶቢስ መናኸሪያ በሚወስደው መንገድ ላይ በክልሉ ፍትህ ቢሮ ፊት ለፊት ነው፡፡

## 3. ተልኮ (Mission)

የከተማችን ፍ/ቤቶች አደረጃጀትና አሰራር ዘመናዊ በማድረግ ከተጽዕኖ ነፃ ሆኖ በሕግ ብቻ የሚሰራ የዳኝነት አካል በመፍጠር በገለልተኝነት በሕዝብ አገልጋይነት በቅልጥፍናና በዘመናዊነት ሕብረተሰብን በማገልገል የዳኝነት ጥራት ቅልጥፍናን እና ሚዛናዊነትን ማረጋገጥ

## 4. ራዕይ (Vision)

በ2020 ፍ/ቤት በሕግ የሚመራ ቀልጣፋ ገለልተኛ ውጤታማ ሚዛናዊና

ጥራት ያለው ፍትህ ለሁሉም ተደራሽ ሆኖ የሚሰጥ ሞዴል ፍ/ቤት ሆኖ ማየት

## 5. እሴቶች፡-

- በውጤት ላይ ያተኮረ ፍትህ አሰጣጥ
- የተገልጋይ እርካታ መዳረሻ ያደረገ የግብ ስኬት
- በቡድን ተቀናጅቶ መሥራት፡-አዳዲስ ሃሣቦችን በመቀበል ልምዶችን ማዳበር
- የሥራ ተነሳሽነት የውሣኔ ጥራትን ማምጣት
- አሣታፊነትና ግልፀኝነት የሰፈነበት አሰራርና ፍትህን ተደራሽ ማድረግ፣
- በሕግ መርህ በመስራት የሕግ የበላይነት ማረጋገጥ
- ታማኝነትና ሚስጥር ጠባቂነት
- መልካም ሥነ-ምግባርና በራስ የመተማመን ላይ የተመሠረተ አገልግሎት አሰጣጥ
- የሕዝብ አገልጋይነት መርህን መከታተል
- የባለድርሻ አካላትን በማሣተፍ እንሰራለን፡፡

## 6 ተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት

## 6.1 ተገልጋዮቻችን

- ከሣሾች
- ተከሣሾች
- የከተማ ሕብረሰተብና ዜጎች
- የከተማ የመንግስት ተቋማት
- ልማታዊ ድርጅቶች
- ጠበቆች ነገረ ፈጆች በልዩ ልዩ ደረጃ የሚገኙ የሕግ ባለሙያዎች
- መንግስታዊና ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ማህበራት ወዘተ

## 6.2 ባለድርሻ አካላት ዝርዝር

- የከተማ ምክር ቤት
- የከተማ አስዳደር ምክር ቤት
- ፍትህና ፀጥታ መምሪያ
- የከተማ ፖሊስ መምሪያ
- ማረሚያ ቤት

- ፍትህ አካላት የሕግ ባለሙያዎች ሥልጠናና ምርምር ማዕከል
- የክልል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ
- መገናኛ ብዙሃን
- የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት
- የሴቶች ሕፃናትና ወጣቶች መምሪያ
- የክልሉ ሥነ-ምግባርና ፀረ-ምስና ኮሚሽን
- የሀዋሣ ዩነቨርሲቲ የሕግ ፋካልቲ
- የሕግ ጠበቆች ማህበር
- ስቪል ሰርቭስ መምሪያ
- የከተማ ገቢዎች ባለስልጣን
- ፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ
- የሐይማኖት ተቋማት
- ብዙኂን ማህበራት

## 7. ተቋማት የሚሰጣቸው አገልግሎቶች ዝርዝር

- በመደበኛ ሥነ-ሥርዓት ሕግ መሠረት የሚቀርቡ የፍ/ር ጉዳዩች
- በተፋጠነ ሥነ-ሥርዓት መሠረት የሚቀርቡ የፍ/ር ጉዳዩች
- በአጭር ሥነ-ሥርዓት መሠረት የሚቀርቡ የፍ/ር ጉዳዩች
- በዐ/ሕግ የሚቀርቡ የመንግስት/ የሕዝብ ጥቅም የሚመለከቱ የፍ/ብሔርና የወንጀል ክስ ጉዳዮች
- ክስ ይዛውር ጥያቄ
- ወጪና ኪሣራ ጉዳዮች
- የአፈፃፀም ክስ
- ተከሣሽ በሌሉበት የተሰጠው ውሣኔ እንዲነሣ የሚቀርብ
- የመጨረሻ ፍርድ ያገኘ የፍ/ብሔር ጉዳይ እንደገና እንዲታይ የሚቀርብ
- የፍ/ብሔር ይግባኝ
- የይግባኝ ማስፈቀጃ
- የወንጀል ቀጥታ ክስ
- እጅ ከፍንጅ ክስ
- ዕድሜአቸው ከ9-15 ያሉ ወጣቶችን በተመከተ የሚቀርቡ

- የመንግስት ጥቅም የሚመለከቱ የደንብ መተላለፍ
- የግል አቤቱታ የሚቀርቡ የወንጀል ጉዳዮች
- ዋስ ለመሆን የሚቀርቡ ጥያቄዎች
- የወንጀል ክስ ይዛወር
- ከሣሽ ተከሣሽ በሌለበት የተሰጠ ውሣኔ እንዲነሣ የሚቀርብ
- የወንጀል ይግባኝ አቤቱታ
- የመያዣና የብርበራ ትዕዛዝ ጥያቄ
- የወንጀል ይግባኝ ማስፈቀጃ
- የጊዜ ቀጠሮ ጥያቄ
- በአመክሮ እንዲለቀቅ
- የውሎ ማስረጃ ጥያቄ
- እገዳ ይነሳልን ጥያቄ
- የመሰየም አቤቱታ
- የዋስትና ይቅረብልኝ ወይም ገንዘብ ይመለስልኝ ጥያቄ
- ሌሎች የተለያዩ አቤቱታዎች ናቸው፡፡

## 8. የተገልጋይ መብት

- ቀልጣፋ ፣ ጥራት ያለውና ፣ እና ተደራሽ የሆነ ሚዛናዊ የዳኝነት አገልግሎት፣

## 9. ከተገልጋዮች የሚጠበቅ ቅድመ ሁኔታዎች

- መብታቸውን የማስጠበቅ የሚቀርቡ ክሶች ዳኝነት ምን እንደሆነ ለይቶ ለሚያሣይ ግልጽ የሚነበብ ሰነዶች ወይም ግልባጭ አሟልቶ ማቅረብ
- በቀጠሮ ቀናት በችሎት በመገኘት የሚሰጡ ትዕዛዞችን ብይኖችን ውሣኔዎች በትክክል ሰምቶ የሚሰማውን ቅሬታ በወቅቱ ማቅረብና መከታተል የችሎት ሥነ-ሥርዓቶችን ማክበር ይጠበቅበታል፡፡
- የፍ/ቤቱን አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓቶችን መረዳትና ማወቅ ለአገልግሎቱ የሚያስፈልጉ ቀዳሚ ሁኔታዎችን አሟልቶ መገኘት

## 10. የባለድርሻ አካላት ፍላጎት

- ቀልጣፋና ውጤታማ የዳኝነት አገልግሎት

- የፈፃሚነትና ተደራሽነት
- የሕግ የበላይነት እንዲረጋገጥ
- ፍትህ ልማትን መልካም አስተዳደርንና ዲሞክራሲን የሚደግፍ እንዲሆን
- መልካም አስተዳደር እንዲሰፍንና እንዲጉለብት
- ዘላቂነት ያለውና የተጠናከረ የዳኝነት አገልግሎት
- የሕብረተሰቡን ፍላጎት መሠረት ያደረገ አገልግሎት

## 11. ስትራቴጂካዊ የትኩረት መስኮች

የትኩረት መስኮችን በቅድሚያ ተልዕኮን፣ራዕይን እና ዓላማን መሠረት በማድረግ የፍርድ አሰጣጥ የትኩረት መስክን ከተገልጋዮ እርካታ፣አመኔታ እና ተጠቃሚነትን ከማሣካት አኳያ ከፋይናንስ አቅርቦት ከአደረጃጀትና ከአመራር ብቃት ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት ያላቸው አሥራ ሦስት ስትራቴጂያዊ ግቦች ተመርጠው ይህንን የትኩረት መስክ ለማሣካት የበለጠ የሚረዱ አምስት ዋና ዋና ዓመታዊ ግቦች ተመርጠዋል፡፡

1. የፍ/ቤቶችን አሰራርና አደረጃጀት ቀልጣፋ ማድረግና ውጤታማነትን ማሣደግ
2. የዳኝነት ነፃነትንና ተጠያቂነትን ማጠናከር
3. የፍ/ቤቶችን ተደራሽነት ማሣደግ
4. የመረጃ አያያዝን አጠቃቀምን ማጠናከር
5. የሰው ኃይልን ማሟላትና ማልማት ናቸው፡፡

## 11.1 የዓመታዊ ግቦች  ዝርዝር ተግባራት

- በሁሉም ፍ/ቤቶች የመሠረታዊ ሥራ ሂደት ለውጡን ቀጣይነትና ዘላቂነት ባረጋገጠ መልኩ ተግባራዊ ማድረግ
- የመረጃ ልውውጥ እንቅስቃሴ የተፋጠነ ለማድረግ የተለያዩ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀምና ያለውን የመረጃ አያያዝ አጠናክሮ መቀጠል
- የፍ/ቤቶች ተደራሽነት የበለጠ ለማረጋገጥ ያሉትን አሠራሮች እንዲሁም አዳዲስ አሰራሮችን መጀመር
- የዳኝነት ነፃነት ተጠያቂነት የሚያረጋግጡ አሰራሮችን ማስፈን
- የተከላካይ ጠበቃ፣ የሕግ ድጋፍና የምክር አገልግሎቶችን ማጠናከርና ማስፋፋት፣

- የፍ/ቤታችን አገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል ደጋፊ ሥራ ሂደቶችን ማጠናከር
- ወቅታዊ እና የተጠናከረ የዳኝነት ሥራ ድጋፍና ክትትል ማካሄድ
- የሰው ኃይል ልማትና አቅም ግንባታ ኘሮግራሞች
- የሕፃናትና የሴቶችን ጥቅማጥቅሞችና መብት ማረጋገጥ
- HIV እና የሥርዓተ ጾታ ሜይንስትሪሚንግ ሥራ ማጠናከር፣
- የሕዝብ ግንኙነትና ንቃተ-ሕግ ሥራዎች ማከናወን
- የሕዝብና የመንግስት ጥቅሞችን ማስጠበቅ
- የተጠናከረ የቅሬታ ማስተናገጃ ሥርዓቶችን መዘርጋት
- የተሟላ የሰው ኃይል አስተዳደር የፋይናንስ የኦዲት ሥራ ሂደቶችን ማጠናከር
- ውጤታማ የልማትና ዕቅድ ግምገማና ግብረ መልስ
- የለውጥና የመልካም አስተዳደር ሠራዊት መገንባትና ማጠናከር
- ቅንጅታዊ አሠራሮችን ማጠናከር
- ተቋማዊ አደረጃጀት ማሻሻልና ማጠናከር

## 12. ከተማ ከፍ/ፍ/ቤት ሥልጣንና ተግባር

የከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በሀገርቱ ሕግና ደንብ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ከሕብረተሰቡ የሚቀርቡትን ጉዳዮች ተቀብሎ ዳኝነት የሚሰጥና የሚያስፈጽም ሆኖ የሚከተሉትን የዳኝነት ሥልጣን አሉት፡፡

1.1 በፍትሐብሔርና በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕጎችና በሌሎች ሕጎች ውስጥ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲያያቸው በተዘረዘሩት ጉዳዮች፣

1.2 በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሥልጣን ሥር የሚወድቁና በውክልና የተሰጡ ጉዳዮች

1.3 አንድ ጉዳይ ከሥሩ ካሉ የመጀመሪያ ደረጃ ወደ ሌላ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ወይም ወደ ራሱ እንዲዛወር በሚቀርብ ጥያቄ

1.4 አንድ ጉዳይ በሥሩ ያሉት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች ሥልጣኖችን አይደለም ብለው የመለሱት እንደሆነ በጉዳዩ ላይ ተገቢው ትዕዛዝ እንዲሰጥበት በሚቀርብ ጥያቄ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡

1.5 ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ከመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይግባኝ የሚቀርብለትን ጉዳይ አይቶ ለመወሰን ሥልጣን አለው፡፡

1.6 የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የፀና ማህበራዊ ፍ/ቤት ውሣኔ የማየት ሥልጣን አለው፡፡

# ክፍል ሁለት

## 2.1 የባለድርሻ አካላት ቁርኝት

| ተ.ቁ | ባለድርሻ አካላት | ለፍ/ቤቱ የሚሰጡት አገልግሎት | አገልግሎት ዓላማ | ጥራት /ደረጃ ተሟልቶ ለቀረበ ጉዳይ 100 %/ | ከተቋሙ የሚጠበቅ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የከተማ ምክር ቤት | ሪፖርቶችን መገምገምና ማጽደቅ | የተሻለ የአሰራር ሥርዓት ለማስፈን | በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት | በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ማቅረብ |
| | | በጀት ለማጽደቅ | የተቋሙን ተልዕኮ ለማሣካት | በጀቱ በታለመለት ዓላማና በስትራቴጂክ ዕቅድ መሠረት | የተቋሙን የሥራና የበጀት ዕቅድ ማቅረብ |
| 2 | የከተማ አስ/ ጽ/ቤት | የሹመት የሚቀርቡ ዕጩ ዳኞች አስተያየት መስጠት | ገለልተኛ የዳኝነት ሥርዓትን ለማስፈን | በሕግና፣ በሕግ ብቻ መሥራት | በሥነ-ምግባር የታነፀ ብቃትና አቅም ያላቸው ዳኞችን መልምሎ ማቅረብ |
| | | ኘሬዝዳንቶች መሾም/ለሹመት ማቅረብ | ለመሾም | በሕግና በሕገ መንግስቱ ተገዥ የሆኑ | ተገቢውን መረጃ ማቅረብ |
| 3 | ፍትህና ፀጥታ መምሪያ | - በምርመራ የተጣራ ክስ ያቀርባል<br>-በዕርቅ የሚያልቁ ጉዳዮች ላይ ድርድር ያደርጋሉ<br>-የሕዝብ ጉዳዮችን በሚመለከት ተቀብሎ ምላሽ ይሰጣሉ | ወንጀል ፈፃሚዎችን ለሕግ ማቅረብ<br>የመንግስትንና የሕዝብን ጥቅም ማስጠበቅ ዘላቂ ሰላም ማምጣት | በሕግ መሠረት | በሕጉ መሠረት ፍትሐዊና ወቅታዊ ውሣኔዎች መስጠት |
| 4 | ፖሊስ መምሪያ | -ወንጀልን መከላከልና መመርመር፣<br>- ፍርድ ቤቱ እንድቀርቡ ትዕዛዝ የሰጠባቸውን ተከታትሎ ማቅረብ፣<br>-የችሎቶች ሥርዓት ማስከበር | ሰላምና ፀጥታ እንዲሰፍን ለማድረግ | በሕግ መሠረት | የክስ አግባብነት መርምሮ ትዕዛዝና ውሣኔ መስጠት |
| 5 | ማረሚያ ቤቶች | -ፍርድ ማስፈጸም<br>-የታራሚዎች ይግባኝ አመክሮ እና ለሎች የመብት ጥያቄዎችን ማቅረብ | -ለማረሚያና ለማነጽ<br>- መብታቸውን ለማስከበር | -በሕጉ መሠረት<br>- የባሕሪይ ለውጥ ለማምጣት | የፍርድ ውሣኔ የተሰጠባቸው እንዲታረሙ መላክ |
| 6 | የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ሥልጠናና የሕግ ምርመር ማዕከል | ቅድሜ ሥራና ድህረ ሥራ ሥልጠና መስጠት | የባለሙያዎችን ብቃት መጨመር ውጥ የሆነ የሕግ አተረጓጓም እንዲኖር ለማድረግ | ብቁ ባለሙያዎችን ማፍራት | መሰልጠን የሚገባቸውን የሕግ ባለሙያዎችን መልምሎ ማቅረብ |
| 7 | የክልል የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ | ዳኞችን ማስተዳደር | የዳኝነት ነፃነትና ተጠያቂነት ማረጋገጥ | ብቃትና ሥነ-ምግባር ያላቸው ዳኞችን ማፍራት | ለተከሰሱ ዳኞች ማስረጃዎችን ማቅረብ ሲወሰንም አፈፃፀሙን መከታተል |
| 8 | ሚዲያ | መረጃ መስጠት | የዳኝነት ነፃነትና ተጠያቂነት ማረጋገጥ | ብቃትና ሥነ-ምግብር ያላቸው ዳኖችን ማፍራት | መድረክ ማመቻቸትና መረጃ መስጠት |

| ተ.ቁ | ባለድርሻ አካላት | ለፍ/ቤቱ የሚሰጡት አገልግሎት | አገልግሎት የሚፈለግበት ዓለማ | ጥራት /ደረጃ ተሟልቶ ለቀረበ ጉዳይ 100 %/ | ከተቋሙ የሚጠበቅ |
|---|---|---|---|---|---|
| 9 | የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች መምሪያ | ለተተኪ ሕፃናትና ሴቶች ድጋፍ መስጠትና ግንዛቤ መፍጠር | የሴቶችና ሕፃናት መብት ማስከበር | የሴቶችና ሕፃናት መብት ማስጠበቅ | የሴቶችና ሕፃናት ጉዳዮች ልዩ ትኩረት መስጠትና የሕፃናት ችሎት ማቋቋም |
| 10 | ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን | ከመንግስት የተሰጣቸውን ሥልጠን አለ አግባብ በተጠቀሙ የመንግስት ሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ላይ ክስ ማቅረብ | በሕገ መንግስቱና በሕጉ መሠረት | በሕጉ መሠረት | በሕጉ መሠረት ፍትሐዊና ወቅታዊ ውሣኔ መስጠት |
| 11 | ከዩነቨርሲቲዎች የሕግ ፋካሊቲዎች | ብቃትና ጥራት ያላቸውን የሕግ ባለሙያዎችን አስተምሮ ማውጣት ለሕብረተሰቡ መሠረታዊ የሕግ ግንዛቤ መስጠት | የፍትህ ጥራት እንዲኖር | ሚዛናዊ የሕግ ትርጉም መስጠት | ብቃት ያለውና ጥሩ ሥነ ምግባር ያለው ባለሙያን መልምሎ መቀበል |
| 12 | የሕግ ጠበቆች | ፍትህ ጥራት ያለው እንዲሆን ሕግን መሠረት ያደረገ ክርክር ማድረግ | ሚዛናዊ ፍትህ ለመስጠት | በሕግ መሠረት | ፈጣን የፍትህ አገልግሎት መስጠት |
| 13 | ሲቪል ሰርቪስ መምሪያ | የተቋሙ ደጋፊ የሥራ ሂደቶች ባለሙያዎች ለመፈጸም የሚረዳ ደንብና መመሪያ አዘጋጅቶ ማቅረብ | የተሟላና ብቃት ያለው ቅጥር ለመፈጸም | በደንቡና መመሪያ መሠረት | የተቋሙ ተልዕኮ ለማስፈጸም |
| 14 | የዞኑ የታክስ ባለስልጣን | የሕዝብና የመንግስት ግብርና ገቢ በተገቢው መሠረት የማይከፍሉ ግለሰቦች ጉዳይ አጣርቶ ማቅረብ | ሕገ- መንግስትና የግብርና ሕጎችን ለማስከበር” | በሕጉ መሠረት | ፍትሐዊና ወቅታዊ ውሣኔ መስጠት |
| 15 | ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ | ወቅታዊና ወርሃዊ የደመወዝና ሥራ ማስኬጃ መስጠት /መክፈል/ | የተቋሙን ዓመታዊ ዕቅድ ለማስፈጸም | መንግስት በፈቀደው መሠረት | ደንቡና መመሪያን መሠረት ያደረገ የወጪ አስተዳደር |
| 16 | የሐይማኖት ተቋማት | ፍትሀዊ ዳኝነት እንዲኖር አስተያየት መስጠት | የሕብረተሰቡ የፍትህ መብት ማስከበር | በለውጥ አሰራር መሠረት ፍትህ እንዲሰጥ | በሕጉ መሠረት ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት ናቸው፡፡ |
| 17 | ብዙኃን ማህበራት | ፈጣንና ቀልጣፋ ፍትህ እንዲኖር አስተያየትና ድጋፍ | የሕብረተሰቡ የፍትህ መብት ማስከበር | በለውጥ አሰራር መሠረት ፍትህ እንዲሰጥ | በሕጉ መሠረት ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት ናቸው፡፡ |

# ክፍል 3

## 3. በክስ  ፍ/ቤት የሚቀርቡ ጉዳዮች

### 3.1 የመደበኛ ፍትሐብሔር ክርክር ላይ የሚፈፀም ሥነ-ሥርዓት

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሉት የሚሰጥበት ስታንደርድ | | ከተገልጋይ የሚጠበቅ ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የሚሰጥበት ሁኔታ | |
| 1 | አቤቱታ / ክስ መዝገቦ መቀበል | ከፍተኛፍ/ቤት፣የመጀመ / ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ | የክሱንና የአቤቱታ ማስረጃዎችን ዝርዝር አሟልቶ በጹሑፍ ማቅረብ |
| 2 | አቤቱታ /ክስ ተቀባይነት ማጣራት | ከፍተኛፍ/ቤት፣የመጀመ / ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ | በቀረበው አቤቱታ ባልተሟሉ ጉዳዮች ጥያቄ ሲቀርብ ምላሽ መስጠት |
| 3 | የዳኝነት ገንዘብ መቀበል | ከፍተኛፍ/ቤት፣የመጀመ / ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ | የዳኝነት ክፍያ መፈጸም |
| 4 | ፋይል መክፈት / ቁጥር መስጠፍ፣ ቁጥር መስጠት ፎርማት መሙላት እና ለባለጉዳይ መስጠት | ከፍተኛፍ/ቤት፣የመጀመ / ደ/ፍ/ቤት | 25 ደቂቃ | ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ | በተዘጋጀው ቦታ ላይ ተቀምጦ ተራውን መጠበቅ |
| 5 | ተከሣሽ ለመከላከያ መልስ ይዞ እንዲቀርብ ትዕዛዝ መስጠት / ቀጠሮ መስጠት | ከፍተኛፍ/ቤት፣የመጀመ / ደ/ፍ/ቤት | ከ2—10 ቀን | መዝገቡ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ | የቀጠሮውን ቀን ሰዓትና ቦታ መዝግቦ መያዝና ትዕዛዞችን መፈጸም |
| 6 | መጥሪያ ፣ በፎርም ሞልቶ ወጪ አድርጎ መስጠት | ከፍተኛፍ/ቤት፣የመጀመ / ደ/ፍ/ቤት | 25 ደቂቃ | መዝገቡ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ | በትክክል ለማድረስ ፈርሞ መቀበል |
| 7 | ከሣሽ ተከሣሽ በቀጠሮ ቀን ሲቀርቡ መልስ መለዋወጥ ለደርድርና ጥያቄ ማቅረብ | ከፍተኛፍ/ቤት፣የመጀመ / ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | በፋይሉ ላይ ክርክር ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ | ለክርክሩ የተሟላ ማስረጃ ይዞ ማቅረቡ ተከሣሽ ያልቀረበ ከሆነም የሰጠበትና ማስረጃ መያዝ መልሱን ከሣሽ መቀበል |
| 8 | ክሱን በንባብ ማሰማት | ከፍተኛፍ/ቤት፣የመጀመ / ደ/ፍ/ቤት | ከ15—20 ደቂቃ | ሰይሞ ማንበብ ከጀመረበት ጊዜ | ከሣሽ ተከሣሽ ክሱን ማስማት |
| 9 | ከሣሽና ተከሣሽ በድርድር ጉዳያቸውን ለመጨረስ ፈቃደኛ ከሆኑ አደራዳሪዎች አማካኝነት ጉዳያቸውን እንዲጭርስ ማድረግ | ከፍተኛፍ/ቤት፣የመጀመ / ደ/ፍ/ቤት | ከ5—10 ቀን | ተከራካሪዎች ከቀረቡበት ጊዜ ጀምሮ | ጉዳያቸውን በዕርቅ ለመጨረስ ፈቃደኛ መሆን የደረሱበትን ደረጃ ለፍ/ቤቱ በቀጠሮ ቀን ማቅረብ |
| 10 | በአደራዳሪዎች አማካኝነት በዕርቅ ከተፈጸመ መጨረሳቸውን በሪፖርት ያቀረቡትን ከመዝገብ ማያያዣና መዝገቡን በትዕዛዝ መዝጋት | ከፍተኛፍ/ቤት፣የመጀመ / ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | ተካራካሪያዋች ከቀረቡበት ጊዜ ጀምሮ | የተፈራረሙበትን የዕርቅ ሰነድ ማቅረብ |

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሉት የሚሰጥበት ስታንደርድ | | ከተገልጋይ የሚጠበቅ ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የሚሰጥበት ሁኔታ | |
| 11 | ዳታ መዝግቦ ወደ መዝገብ ቤት መመለስና ግልባጮችን መስጠት | ከፍተኛፍ/ቤት፣የመጀመ/ ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | ዕርቁ ከችሎት ከተመዘገበበት ጊዜ ጀምሮ | -በዕርቅ ጨርሰው መቅረብ<br>-በችሎት መገኘት<br>- ግልባጮችን መቀበል |
| 12 | ጉዳዩ በዕርቅ የሚያልቅ ከሆነ ተከራካሪዎች ያለመስማማታቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ማያያዝ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ካለ ክስ መልስ እንዲሰጥ ትዕዛዝ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት፣ የመጀመ/ ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | መዝገቡ ከቀረበበት ጊዜ አንስቶ | ያልተስማሙበትን ማስረጃ ማቅረብ<br>- መጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ማቅረብ |
| 13 | ለመልስ በቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ብይን መስጠት | ከፍተኛፍ/ቤት፣የመጀመ/ ደ/ፍ/ቤት | ከ1-2 ቀን | -መዝገቡ ከቀረበበት ጊዜ አንስቶ | ዳኛ ለማጣራት ለሚያቀርባቸው ጥያቄዎች ላይ ምላሽ መስጠት |
| 14 | ተከራካሪ ወገኖችን መመርመር በታመኑ ጉዳዮች ላይ ውሣኔ መስጠት ወይም በአከራካሪ ጉዳዩች ላይ ጭብጥ መያዝ / ማከራከር | ከፍተኛፍ/ቤት፣የመጀመ/ ደ/ፍ/ቤት | 1-2 ሰዓት | መዝገቡ ከቀረበበት ጊዜ አንስቶ | ዳኛ ለማጣራት ለሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች ላይ ምላሽ መስጠት |
| 15 | የከሣሽ ተከሣሽ በተያዘው ጭብጥ ምስክሮች ማሰማት | ከፍተኛፍ/ቤት፣የመጀ/መ/ ደ/ፍ/ቤት | ከ1-2 ሰዓት በእያንዳንዱ ፋይል አንፃር | ምስክሮች ቀርበው መሰማት ከተጀመረ ጊዜ ጀምሮ / በእጅ ጽሑፍ መፃፍ ከተጀመረ ጊዜ ጀምሮ | -ምስክሮች በጭብጡ መሠረት እንዲመሰክሩ ማድረግ<br>- መስቀለኛ ጥያቄ መጠየቅ / ለመጠየቅ መዘጋጀት |
| 16 | የምስክሮች ቃል/ድምጽ/ ወደ ጹሑፍ መቀየር | ከፍተኛፍ/ቤት፣የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | ከ1-4 ሰዓት በአንድ ፋይል | የምስክሮችን ቃል በድምጽ የተቀረጸውን ወደ ጹሑፍ መለወጥ ከተጀመረ ጀምሮ | በቀጠሮ ቀን መገኘት |
| 17 | የማጠቃለያ ሃሣብ ከከሣሽ / ተከሣሽ መቀበል | ከፍተኛፍ/ቤት፣የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | ከ20-30 ደቂቃ | በጹሑፍ ወይም በችሎት መዝገብ መያዝ | በችሎት ቀርቦ መስጠት / ማስመዘገብ/ |
| 18 | ጉዳዩ የይዞታ ክርክር ከሆነ እስከ ቦታው ድረስ እንደአስፈላጊነቱ ሄዶ ማየት | ከፍተኛፍ/ቤት፣የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | ከ1-2 ቀን | መዝገቡ ለውሣኔ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ | ይዞታውን የሚያውቁትን ሽማግሌዎች አሰባስቦ መጠየቅ<br>-ሌሎች አስፈላጊ አካላትን በሥፍራው እንዲያገኙ ትዕዛዝ መስጠት በሥፍራው መገኘት |
| 19 | መዝገቡን መርምሮ ፍርድ መስጠት | ከፍተኛፍ/ቤት፣ የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | ከ5—10 ቀን | መዝገቡ ለውሣኔ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ | በቀጠሮ መገኘት |
| 20 | በዳታ በመመዝገብ ወደ መዝገብ ቤት መመለስ | ከፍተኛፍ/ቤት፣የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | ከ20-30 ደቂቃ | ሂደቱ ሁሉ አልቆ ለዳታው ከተላከበት ጊዜ ጀምሮ | የውሣኔ ግልባጭ መወሰድ |

| 3.2 በአጭር ሁኔታ በሚወሰን ክርክሮች ላይ ስለሚፈም ሥነ-ሥርዓት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቤቱታ /ክስን / መዝገቦ መቀበል | ከፍተኛፍ/ቤት፣ የመጀመ/ ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | ክሱ ከቀረበ በኋላ | የአቤቱታው የክሱን ማስረጃዎችን አሟልቶ ማቅረብ |
| 2 | የአቤቱታው / ክሱን / ተቀባይነት ማጣራት | ከፍተኛፍ/ቤት፣ የመጀመ/ ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | ክሱ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ | ያልተሟሉ ነጥቦች ካሉ ምላሽ መስጠት |
| 3 | በደሃ ደንብ / ዳኝነት መክፍል | ከፍተኛፍ/ቤት፣የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | ክሱ ከተከፈለ ጊዜ ጀምሮ | የዳኝነት ክፍያ መፈጸም |
| 4 | ክሱን መክፈት / ፎርማትን መሙላት ቁጥር መለጠፍ ወይም መሙላት | ከፍተኛፍ/ቤት፣ የመጀመ/ ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | ዳኝነት ከተከፈለ በኋላ | በተሰጠው ቦታ ተቀምጦ መጠበቅ |
| 5 | ተከሣሽ ቀርቦ መከላከል የሚችል መሆኑን በ10 ቀን ውስጥ እንዲያፈቅድ ትዕዛዝ መስጠትና ቀጠሮ መያዝ | ከፍተኛ ፍ/ቤት፣የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | ፋይል ከተከፈተ በኋላ | በችሎት መገኘት |
| 6 | መጥሪያውንና የክሱን አቤቱታውን ወጪ በማድረግ ለከሳሽ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀመ/ ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | ወጪ ትዕዛዝ ከቀረበበት | ፊርሞ መቀበል |
| 7 | የከሣሹ ለመከላከል እንዲፈቀድለት በቃለ መሃላ የሚቀርበውን ማመልከቻ አጣርቶ ለከሣሽ እንዲደርሰው ማድረግ | ከፍተኛፍ/ቤት፣ የመጀመ/ ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | መከላከያ ተስተካክሎ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ | ከችሎት መገኘት<br>መልስ አዘጋጅቶ ማቅረብ |
| 8 | ተከሣሽ ለመከላከያ ያቀረበው የማስፈቀጃ ማመልከቻ ተቀባይነት ካገኘ ወደ መደበኛ ሥነ-ሥርዓት መመለስ ፣ ማስፈቀጃ ተቀባይነት ካጣ መርምሮ መወሰን | ከፍተኛፍ/ቤት፣ የመጀመ/ደ/ፍ/ቤት | ከ2-5 ቀን | ማስፈቀጃ ክሱ ከተጣራ በኋላ | በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት መፈጸም |

## 3.3 በዐ/ሕግ የሚቀርቡ የመንግሥትና የሕዝብን ጥቅም የሚያመላክቱ የፍትሐብሔር ጉዳዮች

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሉት የሚሰጥበት ስታንደርድ | | ከተገልጋይ የሚጠበቅ ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የሚሰጥበት ሁኔታ | |
| 1 | አቤቱታውን መዝግቦ መቀበል | ከፍተኛፍ/ቤት የመጀመ/ ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | አቤቱታ ከቀረበበት | አቤቱታውን አሟልቶ ማቅረብ |
| 2 | አቤቱታውን ተገቢነት ማጣራት | ከፍተኛፍ/ቤት፣ የመጀመ/ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | አቤቱታ ከቀረበበት | በተሰጠው ቦተ ተቀምጦ መከታተል |
| 3 | ፋይል መክፈት / ፎርም መሙላት ቁጥር መስጠፍ/ መፃፍ | ከፍተኛፍ/ቤት፣የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | አቤቱታ ከቀረበ | በተሰጠው ቦታ ተቀምጦ መከታተል |
| 4 | ተከሣሹ ለመከላከ የመልስ ይዞ እንዲቀርብ ትዕዛዝ መስጠት | ከፍተኛፍ/ቤት፣ የመጀመ/ ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | ፋይል ከተከፈተበት ጊዜ ጀምሮ | በተሰጠው ቦታ ተቀምጦ መከታተል |
| 5 | የመከላከያ መልስ የሚቀርብበትን ቀጠሮ መስጠት | ከፍተኛፍ/ቤት፣የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 5-10 ቀን | ቀጠሮ የመስጠት ትዕዛዝ | በተሰጠው ቦታ ተቀምጦ መከታተል |
| 6 | በከሣሽ በኩል ክሱና መጥሪያው ለተከሣሽ እንዲደርስ ማድረግ | ከፍተኛፍ/ቤት፣ የመጀመ/ ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | በፋይል ላይ ትዕዛዝ መስጠት | መጥሪያውን ለተከሣሽ ለማድረስ ፎርም መቀበል |
| 7 | መልስ መለዋወጥና ለድርድር ቀጠሮ መያዝ | ከፍተኛፍ/ቤት፣የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 25 ደቂቃ | ለችሎት መልስ ከቀረበበት | የተሟላ መልስ ይዞ ችሎት መቅረብ |
| 8 | ከሣሽ ተከሣሽ በእርቅ እንዲጨርስ ማግባባትና ማደራደር ወይም በድርድሩ ጊዜ ከተከሣሽ የወሰደውን እንደመልሰ የበደለውን እንድክስ ማድረስ | ከፍተኛፍ/ቤት፣ የመጀመ/ ደ/ፍ/ቤት | ከ5-10 ቀን | ሁለቱም ወገኖች ሲቀርቡ | ከሣሽ ተከሣሽ ችሎት መቅረብና ፍ/ቤቱ ለሚጠይቃቸው ምላሽ መስጠት |
| 9 | ድርድር ሲጠናቀቅ ከሣሽ ተከሣሽና አደራዳሪ እንዲሁም ሌሎች ታዛቢዎች ቢያንስ ሰነዱ ላይ እንዲፈርሙ ማድረግ | ከፍተኛፍ/ቤት፣ የመጀመ/ ደ/ፍ/ቤት | 20-30 ደቂቃ | ግራ ቀኙ ተስማምተው ሲቀርቡ | በድርድሩ ውሣኔ መሠረት በፊርማቸው ማረጋገጥ |
| 10 | በስምምነቱ መሠረት በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ስለመፈጸሙ ከባለመብቱ ማረጋገጫ | ከፍተኛፍ/ቤት፣ የመጀመ/ ደ/ፍ/ቤት | በ10 ቀን ውስጥ | ስምምነቱ ከተፈጸሙ በኂላ | በስምምነቱ መሠረት |
| 11 | በተከሣሽ ራሱ በስምምነቱ መሠረት ከፈፀመ የዕርቅ ባለሙብቱ ከከፈለው የዳኝነት ገንዘብ 50% እንዲመልስለት ማድረግ | ከፍተኛፍ/ቤት፣ የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | ከ20-30 ደቂቃ | በዕርቅ ከተፈጸመ በኂላ | መመለስና የተመለሰለትን መቀበል |
| 12 | በእርቅ መሠረት በጊዜ ገደብ ካልተፈጸመ በባለሙብቱ አመልካችነት ጉዳዩ በአፈፃፀም ሥርዓት መሠረት ተፈፃሚ እንዲሆን ማድረግና ማስፈፀም | ከፍተኛፍ/ቤት፣ የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | ከ2-10 ቀን | በጊዜው ገደብ ውስጥ ካልተፈፀመ ጊዜ ጀምሮ | መከታተል |
| 13 | ዳታ ላይ መመዝገብ ፋይሉ ወደ መዝገብ ቤት እንዲመለስ ማድረግና ኮፒ መስጠት | ከፍተኛፍ/ቤት፣ የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | ግራ ቀኙ ፈፃሚው ከቀረበበት ከቀረቡበት ጊዜ | ግልባጮችን መውሰድ |

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሎት የሚሰጥበት ስታንደርድ | | ከተገልጋይ የሚጠበቅ ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የሚሰጥበት ሁኔታ | |
| 14 | ጉዳዩ በእርቅ ካላለቀ ቀጠሮ በማስያዝ ማስረጃዎቹ እንዲቀርቡ ማዘዝ | ከፍተኛፍ/ቤት፣ የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | በዕርቅ ካላለቀበት ጊዜ ጀምሮ | በችሎት መገኘትና ትዕዛዞችን መፈጸም |
| 15 | ማስረጃዎች የሚቀርቡበትና ቀጠሮ መስጠት | ከፍተኛፍ/ቤት፣ የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | ትዕዛዝ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ | ማስረጃዎችን ይዞ ለመቅረብ ተገቢውን ዝግጅት ማድረግ |
| 16 | ለማስረጃዎች መጥሪያ መስጠት | ከፍተኛፍ/ቤት፣ የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | ትዕዛዝ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ | መጥሪያ ፎርም መቀበልና ማድረስ |
| 17 | ተከራካሪ ወገኖች ቀርበው ተከሣሽ መቃወሚያ ካላቀረበና ካመነ መወሰን | ከፍተኛፍ/ቤት፣ የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | ከ40 ደቂቃ- 1ሰዓት | ተከራካሪዎች ያለመቅረባቸው ሲታወቅ | በችሎትና በማስቻያ ስፍራ ሆኖ ተገቢውን ጥሪ ማድረግ |
| 18 | ተከራካሪ /ግራ ቀኙ/ካልቀረቡ ክሱን መዝጋት | ከፍተኛፍ/ቤት፣ የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | መቃወሚያ ካላቀረበና ክሱን ካመነበት | በችሎት ተገኝቶ ውሣኔ መስጠት |
| 19 | ተከሣሽ ቀርቦ መቃወሚያ ካቀረበ ብይን መስጠት | ከፍተኛፍ/ቤት፣ የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 1 ቀን | መቃወሚያ ካቀረበበት | በችሎት መገኘትና ብይን መስማት |
| 20 | በብይን ክሱ ውድቅ ካልሆነ ፍ/ቤቱ በያዘው ጭብጥ ላይ ግራ ቀኙ ክርክር ማድረግ | ከፍተኛፍ/ቤት፣ የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | ከ40-50 ደቂቃ | መቃወሚያ ካቀረበበት | በችሎት ተገኝቶ ክርክር ማድረግ |
| 21 | በተከራካሪው ወገኖች መመርመርና በታመኑ ጉዳዮች ውሣኔ በመስጠት በተካሄዱ ጉዳዮች ላይ ጭብጥ ማስያዝ | ከፍተኛፍ/ቤት፣ የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 2 ሰዓት | ክሱ ከተሰማ ጊዜ ጀምሮ | የእምነት ወይን ክህደት ቃል ማስመዝገብ |
| 22 | ከሣሽ ተከሣሽ የምስክሮች ቃል መስማት/ በተያዘው ጭብጥ መሠረት ምስክር መስማት | ከፍተኛፍ/ቤት፣ የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 3 ሰዓት | ምስክሮች ከቀረቡ ጊዜ ጀምሮ | ምስክሮችን ማስመስከር |
| 23 | በድምጽ የተቀረጸውን ወደ ጹሑፍ መቀየር | ከፍተኛፍ/ቤት፣ የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 4 ሰዓት በአንድ ጉዳይ | ምስክሮች ቃላቸውን ከሰጡ በኂላ | መከታተል |
| 24 | የክርክር ማቆሚያ ንግግር እንዲያሰሙ ማድረግ | ከፍተኛፍ/ቤት፣ የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | የምስክሮች ቃል ከተሰማ በኂላ | ንግግር ማድረግ ግራ ቀኙ |
| 25 | ውሣኔ መስጠት | ከፍተኛፍ/ቤት፣ የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | ከ2-8 ቀናት | የግራ ቀኙክርክር ካበቃ በኂላ | በችሎት ተገኝቶ ውሣኔውን መስማት |
| 26 | ዳታ መመዝገብ ወደ መዝገብ ቤት መመለስ | ከፍተኛፍ/ቤት፣ የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | ውሣኔ ከተሰጠ በኂላ | የውሣኔ ግልባጮችን /መውሰድ ጥያቄ ማቅረብና መቀበል |
| **3.4** | **የፍትሐብሔር ክስ ይዛወር ጥያቄ** | | | | |
| 1 | አቤቱታ መዝግቦ መቀበልና ፋይል መክፈት | ከፍተኛ ፍ/ቤት፣ | 20 ደቂቃ | አቤቱታ ካቀረበበት ጊዜ አንስቶ | ክስ የሚዛወርበት ምክንያት አሟልቶ ማቅረብ እና ዳኝነት መክፍል |
| 2 | የቀረበውን ማስረጃ ከአቤቱታ ጋር በመመርመር ትዕዛዝ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት፣ | 30 ደቂቃ | አቤቱታ ቀረበበት ጊዜ አንስቶ | ጥያቄ ሲቀርብ ምላሽ /መስጠት |
| 3 | መዝገቡ/ክሱ/ ይዛወር የሚል ትዕዛዝ የተሰ እንደሆነ የሚዛወርበት ፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲደርስ በማድረግ መዝገብ መዝጋት | ከፍተኛ ፍ/ቤት፣ | 30 ደቂቃ | ማስረጃውን ከመረመረ በኂላ | መክታተል |
| 4 | ትዕዛዙን ኮፒ አድርጎ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት፣ | 20 ደቂቃ | ማስረጃውን ከመረመረ በኂላ | ፎርም መቀበል |

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሉት የሚሰጥበት ስታንደርድ | | ከተገልጋይ የሚጠበቅ ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የሚሰጥበት ሁኔታ | |
| **3.5 ወጪና ኪሣራ ክስ አቤቱታ** | | | | | |
| 1 | የወጪና ኪሣራ ጥያቄ ሲቀርብ ውሣኔ ለመስጠት በተሰጠበት መዝገብ ላይ መዝግቦ መቀበል | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | አቤቱታ ከቀረበበት | የተሟላ የወጪና ኪሣራ ዝርዝር ከነማስረጃው ማቅረብ |
| 2 | በቀረበው የወጪና ኪሣራ ክስ መሠረት ባለዕዳው ምላሽ እንዲሰጥ ትዕዛዝ መሥጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀመ/ ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | አቤቱታ ከቀረበበት ጊዜ | መጥሪያውን ማድረስ በችሎት መገኘት |
| 3 | የባለ ዕዳው አስተያየት ወይም መልስ መስማት ወይም መቀበል | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | ተከራካሪ ወገኖች ከቀረቡበት ጊዜ ጀምሮ | በችሎት መገኘት |
| 4 | የግራ ቀኙ ጥያቄና መልስ መሠረት ለቀረበው ኪሣራ ጥያቄ መወሰን | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | ከ2-5 ቀን | ክርክሩ ካበቃበት ጊዜ ጀምሮ | በችሎት መገኘት |
| **3.6 የአፈፃፀም ክስ /አቤቱታ/** | | | | | |
| 1 | የአፈፃፀም አቤቱታ በዋናው መዝገብ ላይ ለዳኝነት መቀበል | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | ከቀረበበት ጊዜ አንስቶ | የተሟላ የአፈፃፀም ክስ ማቅረብ |
| 2 | ለባዕዳው መጥሪያ መላከ ቀጠሮ መያዝ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | ከታዘዘበት ጊዜ ጀምሮ | መጥሪያውን ፎርም መቀበልና ለባለዕዳው ማድረስ |
| 3 | የፍርድ ባለዕዳው ሲቀርብ እንዳይፈርዱ የማይፈጽሙበት ምክንያት ካለ መጠየቅ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | ግራ ቀኙ ከቀረቡበት ጊዜ | ተገቢውን ምላሽ መስጠት |
| 4 | እንደፍርዱ የማይፈጸምበት በቂ ምክንያት ከሌለው እንዲፈጽም ማዘዝ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | በቂ ምክንያት እንደሌለው ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ | በፍርዱ መሠረት መፈጸም |
| 5 | በውሣኔው መሠረት ያልተፈጸመለት መሆኑን የፍርድ ባለመብት ቀርቦ ሲያመለክት ወይም ንብረት ሲያቀርብ እንዲታገድ ትዕዛዝ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | እንደፍርዱ ለመፈጸም ፈቃደኛ ስለመሆነ | የባለዕዳው ንብረት ያለበትንና ዝርዝሩን ለፍ/ቤቱ ማቅረብ |
| 6 | ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ንብረቱን እንዲያግዱ ትዕዛዝ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | ንብረቱ ተለይቶ ከቀረበ በኋላ | የዕገዳ ትዕዛዙን ፎርም መቀበልና ማድረስ |
| 7 | በተከበረው ንብረት ላይ መብት አለን የሚሉ ወገኖች ከቀረቡ ትዕዛዞዝ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | ንብረቱ እንዲከበር ትዕዛዝ ከተሰጠ በኋላ | ንብረቱ የባለዕዳው መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ከአቤቱታው ጋር ማቅረብ |
| 8 | በተከበረው ንብረት ላይ ተቋውሞ ካልቀረበ ወይም ተቋውሞ ቀርቦ ተቀባይነት ካጣ ንብረቱ እንዲሸጥ እንዲገመት ትዕዛዝ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | ንብረቱ ከተከበረ በኋላ | በችሎት ተገኝቶ መከታተል |
| 9 | ንብረቱ እንዲገመትና እንዲሸጥ የታዘዘውን ትዕዛዝ ማስተላለፍ በአመልካቹ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀመ/ ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | እንዳሸጥ ከታዘዘ በኋላ | ንብረቱ ለሚሸጥ ወይም ለሚገምት አካላት ትዕዛዝ |
| 10 | ንብረቱ ተገምቶ የሚርቀርብበትን ጊዜ መወሰን | ከፍተኛ ፍ/ቤት | ከ5-10 ቀን | ንብረቱ እንደተገመተ | አፈፃፀሙን መከታተል |

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሉት የሚሰጥበት ስታንደርድ | | ከተገልጋይ የሚጠበቅ ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የሚሰጥበት ሁኔታ | |
| 11 | ንብረቱ ተገምቶ ሲቀርብ ለሀራጅ እንዲሸጥ ትዕዛዝ መስጠትና አስፈፃሚው መመደብ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | ንብረቱ ከተገመተ በኋላ | በንብረቱ ግምት ላይ በዝቷል ወይም አንሷል |
| 12 | በንብረቱ ግምት አንሷል ወይም በዝቷል በሚል አቤቱታ ላይ ትዕዛዝ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | በሀራጅ እንዲሸጥ ከታዘዘ በኋላ | የጨረታውን አፈፃፀም መከታተል |
| 13 | በንብረቱ ግምት ላይ የቀረበው ተቃውሞ ውድቅ ከተደረገ በኋላ ንብረቱ ከግምቱ መሠረት በሀራጅ እንዲሺጥ ትዕዘዝ መስጠት ፣የሀራጁ አስፈፃሚ መመደብ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | ከ30-50 ደቂቃ | የንብረቱ ግምት ሲቀርብ | መከታተል |
| 14 | የሀራጅ ማስታወቂያ የሚቆይበትን ጊዜ መወሰን | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 1 ወር | ንብረቱ በሀራጅ እንዲሸጥ ከታዘዘ ጀምሮ | የሀራጅ ማስታወቂያ ማድረስ ክፍያ መፈጸም |
| 15 | የሀራጅ አፈፃፀም ሪፖርት ማዘጋጀትና ማቅረብ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 8 ሰዓት | ሀራጅ ከተፈጸመ በኋላ | አፈፃፀሙን መጠበቅ |
| 16 | የሀራጅ አስፈፃሚ ሪፖርት በመቀበል ፍርዱን ማስፈጸም ወይም በሀራጅ መሠረት ያልተፈመበትን በቂ ምክንያት ካለ በድጋሚ የሀራጅ ማስታወቂያ እንዲወጣ ማዘዝ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | ከ40 ደቂቃ እስከ 1 ሰዓት | ሀራጅ ከተፈጸመ በኋላ | አፈፃፀሙን መጠበቅ |
| 17 | ሀራጁ እንደገና እንዲወጣ የታዘዘ እንደሆነ በድጋሜ የሀራጁ ጨረታ ማውጣት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 1 ወር | ድጋሚ ጨረታ ከታዘዘበት | ጹሑፍን ለማተሚያ ድርጅቶች ማድረስ ክፍያ መፈጸም |
| 18 | በ2ኛ ሀራጅ ማስታወቂያ መሠረት የሀራጅ አስፈፃሚውን ሪፖርት እንዲያቀርብ ማድረግ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 8 ሰዓት | የሀራጅ አፈፃፀም ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ | አፈፃፀሙን መከታተል |
| 19 | የሀራጅ አስፈፃሚ ሪፖርት ተግቢነት በማየት የሀራጅ ሽያጭ ማጽደቅ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 1 ሰዓት | የሀራጅ ሪፖርት ከቀረበ በኋላ | አፈፃፀሙን መከታተል |
| 20 | የሀራጅ ሽያጭ በፍ/ቤቱ መጽደቅ ሲረጋገጥ በትዕዛዝ መዝገቡን ዘግቶ ወደ መ/ቤት መመለስ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | ሀራጁ ከጸደቀ በኋላ | አፈፃፀሙን መከታተል |
| 21 | የውሳኔ ግልባጮችን ለተከራካሪ ወገኖች መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | አፈፃፀሙ ከተጠናቀቀ ጊዜ ጀምሮ /ጥያቄ ሲቀርብ/ | ግልባጮችን / ኮፒዎችን መቀበል |

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሉት የሚሰጥበት ስታንደርድ | | ከተገልጋይ የሚጠበቅ ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የሚሰጥበት ሁኔታ | |
| **3.7 ተከሣሽ በሌሉበት የተሰጠ ውሣኔ ለማስነሣት የሚቀርብ አቤቱታ** | | | | | |
| 1 | በሌለበት የተሰጠውን ውሣኔ እንዲነሳ የቀረበውን አቤቱታ መቀበልና ከመዝገቡ ጋር ማያያዝ | ከፍተኛፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | አቤቱታ ከቀረበበት | የቀረበውን ምክንያት ማስረጃ በማሲያዝ |
| 2 | በሌለበት የተሰጠው ውሣኔ እንዲጸና የቀረበውን በፍ/ቤቱ ተቀበይነት ያገኝ እንደሆነ ለመልስ ሰጪው ደርሶት ምላሽ እንዲሰጥ ማዘዝ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | አቤቱታው ተቀባይነት ካገኘበት ጊዜ ጀምሮ | የችሎቱን ትዕዛዝመጠባበቅ |
| 3 | የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ ለመልስ ሰጪው የሚሰጠውን ወጪ አድርጎ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | ትዕዛዝ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ | ትዕዛዙን ፎርም ተቀብሎ ለመልስ ሰጪ ማድረስ |
| 4 | ከመልስ ሰጩ መልስ የሚሰጥበት ቀጠሮ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | ከ5-10 ቀን | ቀጠሮ ከተጠበት ቀን ጀምሮ | የቀጠሮውን ቀን ጠብቆ መገኘት |
| 5 | የከሣሽ/መልስሰጭ አስተያየት መቀበልና ተገቢውን ትዕዛዝ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | ተከራካሪዎች ከቀረቡበት ጊዜ ጀምሮ | በችሎት መገኘት |
| 6 | በሌሉበት በተሰጠው ውሣኔ እንዲነሳ የተፈቀደ እንደሆነ ተገቢውን ኪሣራ ወይም መቀጮ ተከሣሹ እንዲከፍል በማድረግ ወይም ብይኑን በማንሳት ክርክሩ የሚሰማውን ቀን ቀጠሮ መያዝ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | የቀድሞ ውሣኔ /ብይን ከተነሳበት ጊዜ ጀምሮ | ተከሣሹ ኪሣራ ወይን መቀጮ መክፈል፣ወደ ክሱ መግባትና ክርክራቸውን ማካሄድ |
| **3.8 የመጨረሻ ፍርድ ያገኘ የፍ/ብሔር ጉዳይ እንደገና እንዲታይ የሚቀርብ አቤቱታ/358/** | | | | | |
| | | | | | |
| 1 | ውሣኔ እንዲነሣ የቀረበውን አቤቱታ ከመዝገብ ጋር ማያያዝ | ከፍተኛ ፍ/ቤት<br><br>የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | አቤቱታ ከቀረበበት | ፍርድ እንዲነሣ ለቀረበው አቤቱታ አስረጅ ማስረጃን አያይዞ በቃለመሐላ ማቅረብ |
| 2 | ዳግመኛ ዳኝነት እንዲታይ የቀረበውን አቤቱታ ግልባጭ በመላክ መልስ ሰጪው መልሱን እንዲያቀርብ ቀጠሮ መያዝ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 5-7 ቀን | አቤቱታውን ከመዝገብ ጋር ከተያያዘ ጊዜ አንስቶ | ትዕዛዙን ፎርሞ ተቀብሎ ለመለስ ሰጪ ማድረስ” |
| 3 | የመልስ ሰጪውን መልስ መቀበል | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | መልሱ ከቀረበበት ጊዜ | የተሟላ መልስ ከማረጃ ጋር አሟልቶ ማቅረብ |
| 4 | ጉዳዩን መርምሮ ፍ/ቤቱ እንደገና ዳኝነቱ ይታያል አይታይም የሚለውን ትዕዛዝ /ብይን መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 3 ቀን | ማስረጃ ከቀረበበት ወይም ክርክር ካለቀበት ጊዜ | ሙሣኔ /ውጤት/መጠባበቅ |
| 5 | እንደገና መታየት አይገባም ከተባለ መዝገቡን ዳታ እንዲመዘገብ በማድረግ ወደ መ/ቤት መመለስ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | ብይን ወይም ትዕዛዝ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ | የውሣኔ ግልባጭ መውሰድ |

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሉት የሚሰጥበት ስታንደርድ | | ከተገልጋይ የሚጠበቅ ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የሚሰጥበት ሁኔታ | |
| **3.9 የፍትሐብሔር ይግባኝ ቅሬታዎች** | | | | | |
| 1 | የይግባኝ ቅሬታውን መዝግቦ መቀበልና ዳኝነቱን እንዲከፍል ማድረግ | ከፍተኛ ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | ቅሬታው ከመዝገቡ ግልባጭ ጋር ከቀረበበት | የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ሣያልፍ ቅሬታውን አሟልቶ ማቅረብ ዳኝነቱን መክፍል |
| 2 | ፋይል መክፈትና ቁጥሩን ለባለጉዳይ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | ቅሬታውንና የመዝገቡን ግልባጭ ከቀረበበት | የመዝገቡ ቁጥር መቀበል |
| 3 | የቀረውን ይግባኝ መርምሮ ያስቀርባል አያስቀርብም የሚል ትዕዛዝ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት | 3-8 ሰዓት | ጉዳይ /ፋይል ተከፍቶ ከቀረበበት ጊዜ | የዳኛውን ትዕዛዝ መጠባበቅ |
| 4 | መዝገቡ የሚያስቀርብ ከሆነ ያስቀርባል የተባለበትን ነጥብ ዝርዝር በመፃፍ መልስ ሰጪ ለቃል ክርክር ተዘጋጅቶ እንዲቀርበ ማዘዝ | ከፍተኛ ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | መዝገቡ ያስቀርባል ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ | በችሎት መገኘት |
| 5 | የይግባኝ ቅሬታውን ከጥሪው ጋር ለመልስ ሰጪ እንዲደርስ ማድረግ | ከፍተኛ ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | ትዕዛዝ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ | ክፍያውን በመክፈል መጥሪያውን ፈርሞ መቀበልና ማድረስ |
| 6 | መልስ ሰጪ ለቃል ክርክር ፍ/ቤት የሚቀርበበት ቀጠሮ ቀን መወሰን | ከፍተኛ ፍ/ቤት | ከ6-10 ቀን | መልስ እንዲሰጥ ከታዘዘበት ጊዜ ጀምሮ | ቀጠሮ መጠባበቅ |
| 7 | የግራ ቀኙ ተከራካሪዎችን በቃል ማከራከር | ከፍተኛ ፍ/ቤት | 40 ደቂቃ | ተከራካሪ ወገኖች ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ | በችሎት ተገኝቶ የቃል ክርክር ማድረግ |
| 8 | በክርክራቸው መነሻ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ መጥሪያ መፃፍ | ከፍተኛ ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | ተጨማሪ ማስረጃ ማስቀረብ ሲያስፈልግ | የሚፃፈውን ትዕዛዝ መጠባበቅ |
| 9 | በትዕዛዙ መሠረት ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ መጥሪያ ወጪ አድርጐ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | ተጨማሪ ማስረጃ ማስቀረብ ሲያስፈልግ | ትዕዛዙን ለማድረስ ፈርሞ መቀበል |
| 10 | ተጨማሪ ማስረጃ የሚቀርብበት ቀን ቀጠሮ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት | 5 ቀን | ማስረጃ እንዲቀርብ ከታዘዘበት ጊዜ ጀምሮ | መቀበል |
| 11 | ማስረጃዎችን ማሰማት / መቀበል / | ከፍተኛ ፍ/ቤት | ከ1-2 ሰዓት በጉዳዩ | ማስረጃው ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ | ማስረጃውን ይዞ በቅረብ ክርክር ማድረስ |
| 12 | አስፈላጊ ከሆነ ክርክሩ የተነሣበትን ጉዳይ እስከ ስፍራው ድረስ ሄዶ ማየት | ከፍተኛ ፍ/ቤት | ከ1-2 ሰዓት | እስከ ቦታው ድረስ ሄዶ ለማየት ከታዘዘበት ጊዜ ጀምሮ | አስፈላጊው በትዕዛዝ ተቀብሎ ማድረስ በቦታው ሽማግሌዎች ይዞ መጠባበቅ |
| 13 | መርምሮ ውሣኔ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት | 5 ቀን | ክርክሩ ካለቀበት | ውሣኔውን መከታተል |
| 14 | በዳታ መዝግቦ ወደ መዝገብ ቤት መመለስና ግልባጮችን ለተከራካሪ ወገኖች መስጠት እንዲሁም የውሣኔውን ኮፒ ለፍ/ቤቶች መላክ | ከፍተኛ ፍ/ቤት | 1 ቀን | ፍርድ ከተሰጠ በኋላ | ክፍያውን በመፈጸም የውሣኔ ግልባጭ መቀበል |

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሉት የሚሰጥበት ስታንደርድ | | ከተገልጋይ የሚጠበቅ ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የሚሰጥበት ሁኔታ | |
| **3.10 የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ** | | | | | |
| 1 | አቤቱታ መቀበልና ፋይል መክፈት | ከፍተኛ ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | አቤቱታ ከቀረበበት | የይግባኝ መጠየቅያ ጊዜ ያለበትን ከበቂ ማስረጃ ጋር ማቅረብ |
| 2 | አቤቱታውን ከቀረ ማስረጃ ጋር ከማገናዘብ ተገቢውን ትዕዛዝ ማስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | ማስፈቀጃው ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ | በተሰው ቦታ ሆኖ አድርጎ መጠባበቅ |
| 3 | ለአቤቱታ አቅራቢ የተፈቀደለት እንደሆነ በ10 ቀን ውስጥ የይግባኝ ቅሬታውን አዘጋጅቶ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | ከተፈቀደለት ጊዜ ጀምሮ | ማስፈቀጃውን ኮፒ አድርጎ መቀበል አሟልቶ ይግባኝ መክፈት |
| **3.11 የወንጀል ጉዳዮች ክስ** | | | | | |
| 1 | ክስ መዝገቦ መቀበል | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | ክሱ ከቀረበበት | ዐ/ሕግ ክሱን አሟልቶ ማቅረብ |
| 2 | የክሱን አግባብነት ማጣራት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | ክሱ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ | ክሱን መከታተል |
| 3 | ፋይል መክፈት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | ክሱ ከተጠራ በኋላ | መከታተል |
| 4 | ተከሣሹ የሚቀርብበትን ቀጠሮ መያዝ ክሱን ተከሣሽ አንብቦ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ መጥሪያ መላክ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | ከ5-10 ቀናት | ፋይሉ ከተከፈተበት ጊዜ | ትዕዛዙን መጠባበቅ |
| 5 | ለተከሣሹ በቀጠሮ እንዲቀርብ መጥሪያ መላክ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | ትዕዛዝ ከተሰጠበት ጊዜ | መጥሪያውን ተቀብሎ ተሣከሽ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ማድረስ |
| 6 | የተከሣሽ ማንነት ማረጋገጥ ከሣሽ ያቀረበውን ክስ ለተከሣሽ በችሎት በንባብ ማሰማት ክሱን እንደሚቃወም ስለ ወንጀል የእምነት የክህደት ቃሉን እንዲሰጥ ማድረግ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | ተከራካሪዎች ከቀረቡበት ጊዜ ጀምሮ | ከሣሽ ተከሣሽ ተገኝቶ ለጥያቄው ተገቢ ምላሽ መስጠት |
| 7 | ተከሣሽ መቃወሚያ የሚያቀርብ ከሆነ ለቀረበው መቃወሚያ ዐ/ሕግ መልስ ካለው መጠየቅ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | ክሱ ከተነበበ በኋላ | ግራ ቀኙ ለክርክሩ ተዘጋጅቶ መቅረብ |
| 8 | ለቀረበው መቃወሚያ ፍ/ቤቱ አጣርቶ ብይን መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት | ከ1-2 ቀን | ተቃውሞ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ | መከታተል |
| 9 | የተከሣሽ መቃወሚያ ውድቅ የተደረገ እንደሆነ የእምነት ክህደት ቃሉን መመዝገብ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | ክሱ ከቀረበበት | በችሎት በመገኘት ቃሉን መስጠት |
| 10 | ተከሣሽ ድርጊቱን መፈጸሙን በገዛ ፈቃዱ አምኖ ቃሉን የሰጠ እንደሆነ ወዲያውኑ በተከሣሹ ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ይሰጣል | ከፍተኛ ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | ተከሣሽ ሲያምን | ከሣሽ ተከሣሽ የቅጣት አስተያየት መስጠት |

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሉት የሚሰጥበት ስታንደርድ | | ከተገልጋይ የሚጠበቅ ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የሚሰጥበት ሁኔታ | |
| 11 | ተከሣሽ ድርጊቱን ክዶ የተከራከረ ከሆነ ዐ/ሕግ ማስረጃውን አቅርቦ እንዲሰማና ስለተከሣሽ አቆያየት እንዲሰጥ ተደርጎ አስፈላጊውን ትዕዛዝ ይሰጣል | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | ተከሣሽ ክሱን ክዶ ሲገኝ | አስተሰያየት መስጠት |
| 12 | ለምስክሮች መጠሪያ እንዲደርስ ማድረግ መላክ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | ተከሣሽ ክሱን ክዶ ከተከራከረ በኂላ | ዐ/ሕግ ለምስክሮች መጥሪያ መውሰድ |
| 13 | ምስክሮች የሚቀርቡበትን ቀን መወሰን | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | ከ5-10 ቀናት | ትዕዛዝ ከተሰጠበት | ቀጠሮ ቀን መጠባበቅ |
| 14 | ምስክሮች ቃለመሐላ መፈጸም ፣ የቀረበ ምስክሮች የሚመሰክሩበትን ጭብጥ ዐ/ሕግ እንዲይዝ ማድረግና መመዝገብ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | ማስረጃ ከቀረበበት | ምስክሮችን ማቅረብ ጥያቄ መጠየቅ |
| 15 | የከሣሽ ምስክሮች ማሰማት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | ከ1-2 በዓት በየጉዳዩ | ማስረጃ ቀርቦ ጭብጥ ከተያዘ በኂላ | አግባብነት ያላቸውን ጥያቄዎችና መስቀለኛ ጥያቄዎችን መጠየቅ |
| 16 | ከሣሽ ወይም ፍ/ቤቱ ተጨማሪ ማስረጃዎች ማሰማት አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነ ተጨማሪ ማስረጃዎችን እንዲቀርቡ ማዘዝ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | ማስረጃዎች ከተሰሙ በኂላ | መከታተል |
| 17 | ለተጨማሪ ማስረጃዎች መጥሪያ እንዲደርስ መላክ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | ትዕዛዝ ከተሰጠ | ከሣሽ ለተጨማሪ ማስረጃ መጥሪያ መውሰድ |
| 18 | ተጨማሪ ማስረጃ ማሰማት ቀጠሮ መያዝ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 5-10ቀን | ለተጨማሪ ማስረጃ ትዕዛዝ | ተጨማሪ ማስረጃ ማሰማት |
| 19 | የቀረቡትን ተጨማሪ ማስረጃ ማሰማት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 1 ሰዓት | ተጨማሪ ማስረጃዎች ሲቀርቡ | ተጨማሪ ማስረጃ ማሰማት |
| 20 | የምስክሮች ቃል ወደ ጹሑፍ መቀየር | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 1 ቀን | ተጨማሪ ማስረጃ ማሰማት | መከታተል |
| 21 | መርምሮ በነፃ ይሰናበት ወይም ይከላከል ብይን መሰጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 1 ቀን | ማስረጃዎች ከተሰሙ በኂላ | በችሎት መገኘት |
| 22 | ተከሣሹ በእስር ቤት የሚገኝ ከሆነ በነፃ ይሰናበት የሚል ውሣኔ ብይን ከሆነ የመፍቻ ወራንቲ መፃፍና ተከሣሹ እንዲፈታ ማድረግ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 25 ደቂቃ | ብይን ከተሰጠ በኂላ | አፈፃፀም መከታተል |
| 23 | ተከሣሹ ይከላከል ተብሎ እንደሆነ መከላከያ ማስረጃ እንዲቀርቡ ትዕዛዝ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | ተከላከሉ ተብሎ ሲታዘዝ | በችሎት መገኘት |
| 24 | ለመከላከያ ማስረጃ መጥሪያ መፃፍና ወጪ አድርጐ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | ትዕዛዝ ሲሰጥ | ተከሣሹ መጥሪያውን ማድረስ |
| 25 | መከላከያ ማስረጃዎችን ለማሰማት ቀጠሮ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 5-8 ቀን | ትዕዛዝ ከተሰጠ በኂላ | የቀጠሮ ቀን መጠባበቅ |

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሎት የሚሰጥበት ስታንደርድ | | ከተገልጋይ የሚጠበቅ ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የሚሰጥበት ሁኔታ | |
| 26 | ለመከላከያ ማስረጃዎቹን ቃለ መሐላ ማስፈጸም ካሉት ጭብጥ መመዝገብ ማስማት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 2 ሰዓት | ማስረጃዎች ከቀረቡ | ማስማትና አግባብነት ያላቸውን መስቀለኛ ጥያቄዎችን መጠየቅ |
| 27 | የመከላከያ ምስክሮች ቃል ወደ ጹሑፍ ማስቀየር | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 1 ቀን | ማስረጃዎቹ ከተሰሙ በኂላ | አፈፃፀሙን መከታተል |
| 28 | የከሣሽና ተከሣሽ ክርክር ማቆሚያ ንግግር ማስማት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | የምስክሮች ቃል ከተሰማ በኂላ | በችሎት በመገኘት ንግግር ማድረግ |
| 29 | ውሣኔ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | ከ5-8 ቀን | ክርክሩ ካለቀ በኂላ | በችሎት በመገኘት ውሣኔ ማስማት |
| 30 | በተከሣሽ ላይ የጥፋተኝነት ውሣኔ የተሰጠ እንደሆነ ግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የቅጣት አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ማድረግና መመዝገብ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 40 ቀን | የጥፋተኝነት ውሣኔ ከተሰጠ በኂላ | የቅጣት አስተያየት ከቃል ወይም በጹሑፍ መስጠት |
| 31 | የቅጣት ውሣኔ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 1 ሰዓት | የቅጣት አስተያየት ከቀረበ | ከችሎት መገኘት |
| 32 | ቅጣቱ የእስራት ከሆነ የማስሪያዎችን ለማረሚያ ቤቱ መፃፍና ፍርደኛውን ወዲያው ፖሊስ እንዲረከብ ማድረግ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | ትዕዛዝ ከተሰጠ በኂላ | መከታተል |
| 33 | ውሣኔው ተከሣሽን ነፃ የሚያደርግና በማረሚያ ተቋም የሚገኝ ከሆነ የመፍቻ ወራንቲ መፃፍና መላክ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | ከቅጣት ውሣኔ በኂላ | መከታተል |
| 34 | ውሣኔው የገንዘብ መቀጮ ከሆነ ወዲያውኑ የቅጣቱን ገንዘበ ማስከፈል ካልተከፈለ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲከፍል ዋስትና በመቀበል እንዲለቀቅ ማድረግ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | ከቅጣት ውሣኔውና ከትዕዛዝ በኂላ | የተወሰነውን የገንዘብ መቀጮ መክፈል |
| 35 | ዳታ በመመዝገብ መዝገቡን ወደ መዝገብ ቤት መመለስ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | ጉዳዩ ካለቀ በኂላ | የውሣኔ ግልባጭ መውሰድ |
| **3.12 የእጅ ከፍንጅ ወንጀል ጉዳዮች** | | | | | |
| 1 | ክሱን በመቀበል ፋይል መክፈት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | ክሱ ከቀረበበት በኂላ | ክሱንና ማስረጃውን አሟልቶ ማቅረብ |
| 2 | ክሱን ሰምቶ መወሰን | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 1 ቀን | ክሱ ሲቀርብ | በችሎት መገኘት |
| 3 | ውሣኔው የእስራት ቅጣት የሆነ እንደሆነ ወራንት ጽፎ መላክ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | ውሣኔ ከተሰጠ በኂላ | መከታተል |
| 4 | ዳታ መመዝገብ መዝገቡን ዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት መመለስ የውሣኔ ኮፒ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | ውሣኔ ከተሰጠ በኂላ | የውሣኔ ኮፒ መውሰድ |

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሎት የሚሰጥበት ስታንደርድ | | ከተገልጋይ የሚጠበቅ ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የሚሰጥበት ሁኔታ | |
| **3.13 ዕድሜቻው 9-15 ያሉ ወጣ** | | | | | |
| 1 | የወንጀሉን አቤቱታ መዝግቦ መቀበል | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | አቤቱታ ሲቀርብ | አቤቱታውን ክሱን አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ይዞ ማቅረብ |
| 2 | የአቤቱታውን ተቀባይነት ዕድሜው አጠራጣሪ ከሆነ ማስመርመር ወንጀሉ ከ10 ዓመት ከላይ የሚያስቀጣ መሆንና አለመሆኑን እና የቅርብ ዘመዶች መኖራቸውን ማጣራት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 1-3 ሰዓት | አቤቱታ ሲቀርብ | አፈፃፀሙ መከታተል |
| 3 | ፋይል መከፈትና ልጁን ያመጣውን ሰው ስለልጅ ዝርዝር ማስረጃ እንዲሰጥ ማድረግ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | አቤቱታ ሲቀርብ | ፍ/ቤቱ ለሚጠይቀው ጥያቄዎች ማብራሪያ መስጠት |
| 4 | በሕፃኑ አቆያየት ላይ መወሰን /ማን ይቆያል ፣ለወላጅ ለዘመዶቹ ፣ ለበጎ አድራጊ ድርጀቶች የሚለውንና ፖሊስ ምርመራ እንዲያደርግ ማዘዝ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 40 ደቂቃ | | |
| 5 | በታክቲክና በቴክኒክ ማስረጃ በመለየት ለፍርድ ቤት ማቅረብ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | ከ3-5 ቀን | ትዕዘዝ ሲሰጥ | የተጠየቀውን ማስረጃ አሟልቶ መገኘት |
| 6 | ከ10 ዓመት በላይ የሚያማስቀጣ ወንጀል ስለመሆኑ ከተረጋገጠ ክስ ማቅረብ ለሕፃኑ ድጋፍ /ጠበቃ/ ማቆም 10 ዓመት በታች የሚያስቀጣ ከሆነ ጊዜ ክስ መመስረት ሣያስፈልግ ማስረጀ ሰምቶ መወሰን | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 3 ቀን | ክሱ ሲቀርብ | በስረጃ የተደገፈ ክስ ማቅረብና ማሰማት |
| 7 | ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጣው ወንጀል ከሆነ ክስ የሚሰማበት ጊዜ መወሰንና ለማስረጃዎች ማዘዝ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | ምርመራ ሲያልቅ | ችሎቱን መከታተል |
| 8 | ማስረጃ የሚሰማበትን ቀጠሮ መያዝ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | ከ5-8 ቀን | ትዕዛዝ ሲታዘዝ | መጠበቅና ማቅረብ |
| 9 | በዝግ ችሎት ክሱ ተነቦለት መልስ እንዲለዋወጡ መጠየቅ ሙሉ በሙሉ ካመነ የጥፋተኝነት ውሣኔ መሰጠት ካላመነ የሁለቱም ወገን ማስረጃ ማሰማት የግራ ቀኝ ማስረጃ ፍ/ቤቱ መመርመር | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 4 ሰዓት | ክስ ከቀረበበት | ማስረጃ ማሰማት |
| 10 | የተቀረጸውን ድምጽ ወደ ጹሑፍ መመለስ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 1 ቀን | ማስረጃ ከተሰማ በኂላ | መከታተል |
| 11 | መርምሮ የጥፋተኝነት ውሣኔ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 2 ቀን | ክርክር ሲያልቅ | በችሎት መገኘት |
| 12 | በቅጣት ላይ አከራክሮ መወሰን ማስጠንቀቅያ ለሕፃኑ ለወላጆቹ መስጠት፣ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 1 ሰዓት | ከተወሰነ በኂላ | ችሎቱንመከታተል |
| 13 | ዳታ በመመዝገብ መዝገቡን ዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት መመለስ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | ከተወሰነ በኂላ | የውሣኔው ግልባጭ መውሰድ |

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሉት የሚሰጥበት ስታንደርድ | | ከተገልጋይ የሚጠበቅ ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የሚሰጥበት ሁኔታ | |
| **3.14 የሕዝብና የመንግስት ጥቅም የሚመለከቱ የደንብ መተላለፍ** | | | | | |
| 1 | ክስ መዝግቦ መቀበልና ፋይል መክፈት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | ክሱ ሲቀርብ | የክሱን ማስረጃዎችን አሟልቶ ማቅረብ |
| 2 | መዝገቡን መርምሮ ትዕዛዝ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | ክሱ ሲቀርብ | ችሎት በመገኘት ትዕዛዙን መከታተል |
| 3 | ቀጠሮ መያዝ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | ከ3-8 ቀን | ትዕዛዝ ሲሰጥ | መከታተል |
| 4 | መጥሪያውን ከክሱ ጋር ለተከሣሹ እንዲያደርስ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | ትዕዛዝ ከተሰጠ በኋላ | መጥሪያውን ፈርሞ መውሰድ |
| 5 | በአንድነት የቀረበውን ማስረጃ መስማትና መከላከያ በመስማትና ተገቢውን ውሣኔ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | ከ2-6 ቀናት | አቤቱታው ሲደረስ | በችሎት በመገኘት ክርክር ማስማት |
| 6 | ውሣኔው የገንዘብ ከሆነ ወዲያውኑ ማስከፈል ፣እስራት ከሆነ ወራንቲ ቆርጦ መላክ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 2 ሰዓት | ውሣኔው ከተሰጠ በኋላ | የውሣኔውን ገንዘብ መቀጮ መክፍል |
| **3.15 በልግ አቤቱታ የሚቀርቡ የወንጀል ጉዳዮች** | | | | | |
| 1 | አቤቱታውን መዝግቦ መቀበል | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 25 ደቂቃ | አቤቱታ ሲቀርብ | አቤቱታ አሟልቶ ማቅረብ |
| 2 | የአቤቱታውን አግባብነት / ተቀባይነት/ በይርጋ አለመታገዱን በግል የሚቀርቡ ስለመሆኑ ማጣራት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | አቤቱታ ሲቀርብ | መከታተል |
| 3 | የወንጀል ፋይል መክፈትና ለባለጉዳይ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | አቤቱታ ሲቀርብ | የፋይል ቁጥር መውሰድ |
| 4 | ተከሣሽ እንዲቀርብ ትዕዛዝ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | ፋይል ከተከፈተ በኋላ | መከታተል |
| 5 | ክርክሩን ለመስማት ቀጠሮ መያዝ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | ከ3-8 ቀን | ቀጠሮ ሲሰጥ | መጠባበቅ |
| 6 | መጥሪያ ውጪ አድርጎ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | ትዕዛዝ ሲሰጥ | መጥሪያ እንዲበቀል ማድረግ |
| 7 | ግራ ቀኙ ወገኖች ሲቀርቡ በዕርቅ ለመጨረስ እንደሚፈልጉ እንዲሁም የእርቁን ጠቀሜታ የተጓዳኝና ለተጠርጣሪን መብትና ግዴታ በማስገንዘብ በድርድር እንዲያልቅና እንደአስፈላጊነቱ እንዲክሱ ማድረግ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 1 ሰዓት | ተከራካሪ ወገኖች ስምምነት | በዕርቅ በድርድር ለመጨረስ ፈቃደኛ መሆናቸውን መግለጽ |
| 8 | በድርድር ካላለቀ ቀጠሮ በመያዝ ተከራካሪዎቹ ማስረጃዎቻቸውን እንዲያቀርቡ ማዘዝ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | በዕርቅ ካላለቀ | አፈፃፀም መከታተል |
| 9 | ማስረጃ ለማሰማት ቀጠሮ መያዝ ምስክሮችንና መከላከያ ምስክሮችን በአንድነት መስማት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | ከ4-6 ሰዓት | ትዕዛዝ ሲሰጥ | ቀጠሮ መከታተል |
| 10 | ምስክሮች ቀርበው መከላከያ ማስረጃ ያልቀረበ ከሆነ ለመ/ምስክር ትዕዛዝ ማዘጋጀት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | ትዕዛዝ ሲሰጥ | መጥሪያውን ለምስክሮች መስጠት |

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሉት የሚሰጥበት ስታንደርድ | | ከተገልጋይ የሚጠበቅ ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የሚሰጥበት ሁኔታ | |
| 11 | ምስክሮች የምስክርነት የመከላከያ ቃላቸውን እንዲሰጡ ማድረግ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | ከ1-2 ሰዓት በአንድ ጉዳይ | ምስክሮች ቀርበው ቃላቸውን መስጠት ከጀመሩበት | ምስክሮችን ማስመስከር መስቀለኛ ጥያቄ መጠየቅ |
| 12 | ምስክርነት ቃል ወደ ጹሑፍ መቀየር | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 4 ሰዓት | የምስክር ቃል ከተሰጠ በኋላ | መከታተል |
| 13 | የክርክር መቃወሚያ ንግግር እንዲያደርጉ ማድረግ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | የማስረጃዎች ቃል ከተሰማ በኋላ | መከታተል |
| 14 | መርምሮ ውሣኔ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 5 ቀን | ክርክር ሲያልቅ | በችሎት መገኘት |
| 15 | ውሣኔውን የቅጣት የሆነ እንደሆነ ትዕዛዙን መጻፍና ወራኒት ወጪ ማድረግ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 10ደቂቃ | ውሣኔ ሲሰጥ | መከታተል |
| 16 | የገንዘብ መዋጮ ከሆነ ወዲያውኑ በማስከፈል መልቀቅ ወዲያውኑ ካልተከፈለ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲከፈል በዋስትና መልቀቅ ወይም ሌላ በአማራጭ መቅጣት/መወሰን | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | ውሣኔ ሲሰጥ | መቀጫውን መክፈል |
| 17 | ተከሣሽ በውሣኔው ነፃ ከሆነና ክሱ የቀረበው በከሣሽ ወጪ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን የተከሣሽ ውጪ እንደአስፈላጊነቱ እንዲሸፍን ማድረግ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | በውሣኔ ተከሣሽ ነፃ ሲሆን | ወጪውን ጠይቆ መቀበል የተከሣሽን ወጪ መክፈል |
| 18 | ዳታ መመዝገብ ወደ መ/ቤት መመለስ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | ውሣኔ ሲያልቅ | የውሣኔው ግልባጭ መውሰድ |
| **3.16 ዋስ ለመሆን የሚቀርብ ጥያቄ/አቤቱታ** | | | | | |
| 1 | ዋስ ለመሆን የሚቀርብ ጥያቄ አቤቱታ መቀበል | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | አቤቱታ ሲቀርብ | ለዋስትና አስፈላጊ የሆኑ አሟልቶ ማቅረብ |
| 2 | የቀረበው ማስረጃ ለዋስትና በቂ መሆኑን መመርመር | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | አቤቱታ ሲቀርብ | |
| 3 | ለዋስትና የቀረበው ነገር ተቀባይነት ሲያገኝ ለመያዣ የቀረበው ንብረት ወይም ገንዘብ ገቢ እንደሆነ ወይም ንብረቱ ከሆነ ታግዶ እንዲቆይ ማዘዝ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | ማስረጃ ከመረመረ በኋላ | መፃፍ ምላሽ ማምጣት ግዴታ መግባት |
| 4 | ንብረቱ መታገዱ ሲያረጋግጥ በዋስትና እንዲለቀቅ ትዕዛዝ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | | መከታተል |
| 5 | ትዕዛዙን ወጪ አድርጎ መስጠት /በዋስትና የሚያልቅበት ሁኔታ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | ንብረቱ ከታገደ ከተያዘ በኋላ | መከታተል |

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሉት የሚሰጥበት ስታንደርድ | | ከተገልጋይ የሚጠበቅ ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የሚሰጥበት ሁኔታ | |
| **3.17 የወንጀል ክስ ይዛወር አቤቱታ** | | | | | |
| 1 | አቤቱታ መዝግቦ መቀበልና እንደአስፈላጊነቱ ፋይል መክፈት | ከፍተኛ ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | አቤቱታ ሲቀርብ | ክሱ ይዛወር የተባለበት ምክንያት ማቅረብ |
| 2 | ማስረጃውን ከአቤቱታ ጋር በመመርመር ትዕዛዝ | ከፍተኛ ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | አቤቱታ ሲቀርብ | |
| 3 | መዝገቡ ይዛወር የሚል ትዕዛዝ የተሰጠ እንደሆነ ለሚዛወርበት ፍ/ቤት እንዲያውቅ ማድረግ | ከፍተኛ ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | ይዛወር ትዕዛዝ ከተሰጠ በኋላ | የዝውውሩን ትዕዛዝ ማድረስ |
| **3.18 የወንጀል ይግባኝ አቤቱታዎች** | | | | | |
| 1 | ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የቀረበውን ይግባኝ መዝግቦ መቀበል | ከፍተኛ ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | ቅሬታው ሲቀርብ | የተሟላ ይግባኝ ማቅረብ |
| 2 | መርምሮ ተቀባይነቱን ማጣራት/ የይግባኙ/ጊዜ ያላለፈ ወዘተ | ከፍተኛ ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | ቅሬታው ሲቀርብ | የተሟላ ይግባኝ ማቅረብ |
| 3 | ዳኝነት አስከፍሉ ፋይል መክፈት የፋይል/ቁጥር መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | ጉዳዩ ሲሰጠው | ዳኝነት መክፈል ፋይል ቁጥር መውሰድ |
| 4 | ይግባኝ መርምሮ ያስቀርባል አያስቀርብም የሚል ትዕዛዝ መስጠት ጉዳይ ዋስትና የማይከለከል ከሆነ የሥር ውሣኔ አግዶ በዋስትና ማቆየት ያስቀርባል የተባለበት ነጥብ ዝርዝር መግለጽ | ከፍተኛ ፍ/ቤት | ከ2-6 ሰዓት | ፋይል ከተከፈተ በኋላ | መከታተል |
| 5 | ይግባኙን ለመስማት ቀጠሮ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት | ከ5-10 ቀን | ሲታዘዝ | መከታተል |

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሎት የሚሰጥበት ስታንደርድ | | ከተገልጋይ የሚጠበቅ ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የሚሰጥበት ሁኔታ | |
| 6 | መጥሪያውን ጽፎ ከይግባኝ ቅሬታው ጋር እና ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ ጋር መላክ | ከፍተኛ ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | ሲታዘዝ | መጥሪያውን ፈርሞ መውሰድ ማድረስ |
| 7 | ግራ ቀኙ ሲቀርብ የቃል ክርክራቸውን መስማት ተጨማሪ ማስረጃም ካስፈለገ መስማት | ከፍተኛ ፍ/ቤት | 1 ሰዓት | ተከራካሪ ወገኖች ሲቀርቡ | ክርክር ማድረግ |
| 8 | መርምሮ ውሣኔ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት | ከ3-5 ቀን | ክርክሩ ሲያልቅ | ችሎት ተገኝቶ መከታተል |
| 9 | ውሣኔውን የእስራት ቅጣት የሚያስከትል ከሆነ ፍርደኛው ወጪ ከሆነ የማስሪያ ትዕዛዝ መስጠት ወራንት መስጠት፣ ማረሚያ ተቋም ማስረከብ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | ከ1-2 ሰዓት | የቅጣት ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ | ችሎት ተገኝቶ መከታተል ያለበትን አድራሻ |
| 10 | ዳታ መዝግቦ የውሣኔ በግልባጭ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ | ለፖሊስ መጠቆም የውሣኔ ግልባጭ መውሰድ |
| **3.19 የወንጀል ይግባኝ ማስፈቀጃ** | | | | | |
| 1 | አቤቱታውን መዝግቦ መቀበል | ከፍተኛ ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | አቤቱታ ሲቀርብ | ጊዜው ያለፈበት ምክንያት ከመግለጽ ጋር ማቅረብ |
| 2 | የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ትዕዛዝ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | አቤቱታ ሲቀርብ | መከታተል |
| 3 | አቤቱታውን ተቀብይነትን ያገኘ እንደሆነ ቅሬታውን የሚቀርብበትን ቀን መወሰንና ሲቀርብ መወሰን | ከፍተኛ ፍ/ቤት | ከ3-5 ቀን | ትዕዛዝ ከተሰጠበት | በትዕዛዙ መሠረት መፈጸም |
| 4 | ዳታ መመዝገብ ወደ መዝገብ ቤት መመለስ | ከፍተኛ ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | ትዕዛዝ ከተሰጠበት | የትዕዛዙ ግልባጭ መውሰድ |
| **3.20 በአመክሮ እንዲያልቅ የሚቀርቡ አቤቱታ** | | | | | |
| 1 | አቤቱታውን መዝግቦ መቀበል | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | አቤቱታ ሲቀርብ | አቤቱታውን ከማረሚያ ቤቱ ተሟልቶ ማቅረብ |
| 2 | አቤቱታው ከዋና መዝገብ ጋር ተገናዝቦ ሲቀርብ ትዕዛዝ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | ፋይል ከቀረበበት ጊዜ | መከታተል |
| 3 | አመክሮ ታይቶ የተፈቀደ እንደሆነ ታራሚው እንዲፈታ ለማረሚያ ተቋም ትዕዛን መፃፍ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | ከ1-2 ሰዓት | አመክሮ ታሣቢ ሲሆን | ጉዳዮን መከታተል |
| 4 | ዳታ መመዝገብ ወደ መ/ቤት መመለስ ኮፒ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | ውሣኔ ው ሲያልቅ | የውሣኔ ግልባጮች መውሰድ |
| **3.21 ይግባኝ ከከፍተኛ ፣ ወደ ጠቅላይ ሲጠየቅ ወይም ወደ ላይ ፍ/ቤት ሲጠይቅ** | | | | | |
| 1 | ይግባኝ የተባለበትን አቤቱታውን መቀበል | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | አቤቱታ ሲቀርብ | አቤቱታውን ማቅረብ |
| 2 | የሚገለብጠውን ቀጥታ ክስ ከሆነ ወደ ኦፊሰር መምራት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | አቤቱታ ሲቀርብ | መከታተል |
| 3 | የሚያልቅበት ቀጠሮ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | ከ5 ሰዓት - 2 ቀን | ከተመራበት ጊዜ ጀምሮ | መከታተል |
| 4 | ግልባጭ አልቆ ለተገልጋይ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 30 ደቂቃ | ከተመራበት ጊዜ ጀምሮ | ወጪ ሆኖ መቀበል |

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሉት የሚሰጥበት ስታንደርድ | | ከተገልጋይ የሚጠበቅ ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የሚሰጥበት ሁኔታ | |
| **3.22 የተለያዩ አቤቱታዎች** | | | | | |
| 1 | አቤቱታውን መቀበልና ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ማዘዝ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | አቤቱታ ሲቀርብ | የሚፈልገውን ጉዳይ በትክክል አሣይቶ ማቅረብ |
| 2 | ምላሹን ማዘጋጀት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | አቤቱታ ሲቀርብ | መከታተል |
| 3 | ወጪ ተደርጎ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | አቤቱታ ሲቀርብ | መከታተል/መጠባበቅ/ |
| **3.23 የመሰየም አቤቱታ** | | | | | |
| 1 | አቤቱታውን መቀበልና እንደ አስፈላጊነቱ ፋይል መክፈት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | አቤቱታ ሲቀርብ | አቤቱታውን አሟልቶ ማቅረብ |
| 2 | አቤቱታውን መርምሮ ትዕዛዝ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 1 ሰዓት | ፋይል ሲቀርብ | መከታተል |
| 3 | ዳታ መመዝገብና ለፍ/ቤቶች የውሣኔ ግልባጭ በመላክ መዝገቡን ዘግቶ ወደ መ/ቤት መመለስ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | ውሣኔ ሲያልቅ | የውሣኔ ግልባጮችን መውሰድ |
| **3.24 የመያዣና ብርበራ ትዕዛዝ ጥያቄ** | | | | | |
| 1 | አቤቱታውን መርምሮ መቀበል | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | አቤቱታ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ | ተገቢ መረጃና ጥያቄ ማቅረብ |
| 2 | ፋይል አዘጋጅቶ መክፈት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | አቤቱታ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ | መከታተል |
| 3 | መርምሮ ትዕዛዝ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | ፋይል ከተከፈተበት ጊዜ አንስቶ | መከታተልና ትዕዛዝ መውሰድ |
| 4 | ትዕዛዞችን በፎርም ሞልቶ ወጪ አድርጐ መስጠትና መዝገቡን መዝጋትና መመለስ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | ትዕዛዝ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ | ለፍ/ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ |
| **3.25 የጊዜ ቀጠሮ ጥያቄ** | | | | | |
| 1 | አቤቱታ መርምሮ መቀበልና ፋይል መክፈት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | አቤቱታ ሲቀርብ | ተገቢ መረጃና ጥያቄ ማቅረብ |
| 2 | በመዝገቡ በዳኞች ትዕዛዝ መሰጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | መዝገቡ ሲቀርብ | መከታተል |
| 3 | ትዕዛዙን በፎርም ሞልቶ ወጪ አድርጐ መስጠትና መዝገቡን በፎርማት መዝግቦ መመለስ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | ከትዕዛዝ በኋላ መዝገቡ ሲቀርብ | ትዕዛዙዝ ተከታትሎ መውሰድና ለፍ/ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ |
| **3.26 የውሎ ማስረጃ ጥያቄ** | | | | | |
| 1 | አቤቱታ መርምሮ መቀበልና ከፋይል ጋር ማያያዝ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | አቤቱታ ሲቀርብ | ከተገቢው መረጃ ጋር ጥያቄ ማቅረብ |
| 2 | መርምሮ ትዕዛዝ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | ፋይል ሲቀርብ | መከታተል |

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሉት የሚሰጥበት ስታንደርድ | | ከተገልጋይ የሚጠበቅ ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የሚሰጥበት ሁኔታ | |
| 3 | ትዕዛዙን በፎርም ሞልቶ ወጪ አድርጎ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | ከትዕዛዝ በኋላ ፋይል ሲቀርብ | ተከታትሎ መውሰድ |
| 4 | ፋይሉን በዳታ ቤዝ ሞልቶ መመለስ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | ከትዕዛዝ በኋላ ፋይል ሲቀርብ | ተከታትሎ መውሰድ |
| **3.27 ዕግድ ይነሣልኝ ጥያቄ** | | | | | |
| 1 | አቤቱታውን መርምሮ መቀበልና ከፋል ጋር ማያያዝ ለዳኞች ማቅረብ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | አቤቱታው ሲቀርብ | ተከታትሎ ትዕዛዝ መውሰድ |
| 2 | መርምሮ ትዕዛዝ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 15 ደቂቃ | ፋይል ሲቀርብ | ተከታትሎ ትዕዛዝ መውሰድ |
| 3 | ትዕዛዙን በፎርም መሙላትና ወጪ አድርጎ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | ከትዕዛዝ በኋላ ፋይል ሲቀርብ | ተከታትሎ ትዕዛዝ መውሰድ |
| 4 | መዝገቡን በዳታ ቤዝ መዝግቦ ወደ መ/ቤት መመለስ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | ከትዕዛዝ በኋላ ፋይሉ ሲቀርብ | ተከታትሎ ትዕዛዝ መውሰድ |
| **3.28 ዋስትና ይቀየርልን ወይም ገንዘብ ይመለስልኝ ጥያቄ** | | | | | |
| 1 | አቤቱታ መርምሮ መቀበልና ከፋይል ጋር አያይዞ ለዳኞች ማቅረብ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | አቤቱታ ሲቀርብ | ትዕዛዝ ተከታትሎ |
| 2 | መርምሮ ትዕዛዝ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | ፋይሉ ከተገቢው አቤቱታ ጋር ሲቀርብ | ትዕዛዝ መውሰድ ለሚመለከተው መድረስና ምላሽ መስጠት |
| 3 | ትዕዛዝ በፎርም ሞልቶ ወጪ አድርጎ ለባለጉዳይ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | ከትዕዛዝ በኋላ መዝገቡ ሲቀርብ | ትዕዛዝ መውሰድ ለሚመለከተው መድረስና ምላሽ መስጠት |
| 4 | መዝገቡን መረጃ ተይዞ ወደ መ/ቤት መመለስ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | ከትዕዛዝ በኋላ መዝገቡን ሲቀርብ | ትዕዛዝ መውሰድ ለሚመለከተው መድረስና ምላሽ መስጠት |
| **3.29 ቅሬታ ማስተናገጃ ሥርዓቶች** | | | | | |
| 1 | ቅሬታዎችን በጹሑፍ፣በቃል፣በስልክ ማቅረብ | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | ቅሬታ ሲቀርብ | ቅሬታውን ከተገቢው መረጃ ጋር ማቅረብ |
| 2 | ቅሬታውን መርምሮ ምላሽ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት | 20 ደቂቃ | ቅሬታው ከቀረበ በኋላ | መከታተል |
| 3 | ምላሹን በጹሑፍ ወይም በቃል ማዘጋጀት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት | 25 ደቂቃ | ቅሬታው ከቀረበ በኋላ | መከታተል |
| 4 | ምላሹን በጹሑፍ ወይም በቃል አዘጋጅቶ መስጠት | ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት | 10 ደቂቃ | ቅሬታው ከቀረበ በኋላ | ምላሹን መቀበል |

## 4. ለተገልጋዮች የምንገባው ቃል

- ❖ በቻርተሩ ውስጥ በተቀመጠው ስታንደርድ መሠረት ለዜጎች ተደራሽ፣ ተአማንነት ያለውን ቀልጣፋ አገልግሎት እንሰጣለን፡፡
- ❖ ተገልጋይ ተኮር የሆነ ፈጣን አገልግሎት እንሰጣለን፡፡
- ❖ በራሳቸው ጠበቃ ማቆብ ለማይችሉት የተከላካይ ጠበቃ አገልግሎት እንሰጣለን፡፡
- ❖ ተገልጋዮችን በአክብሮት በፍትሀዊነትና በእኩልነት ያለ አድሎ እናገለግላለን፡፡
- ❖ አቅም ለሌላቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች የቅድሚያ አገልግሎት ካርድ እናዘጋጃለን፡፡
- ❖ ነፃ ገለልተኛ ግልጽኝነትና ተጠያቂነት ያለውን ዳኝነት እንሰጣለን፡፡
- ❖ አገልግሎት አሰጣጣችን ላይ ለተገልጋይ ትምህርት በመስጠት ግንዛቤ እንፈጥራለን፡፡
- ❖ .ተገልጋዩ አመኔታ እርካታና ተጠቋሚነትን እናረጋግጣለን፡፡

## 5. የተገልጋዮች መብት

- ➢ ፍ/ቤቱ ባስቀመጠው የጥራት ደረጃዎችና የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ መሠረት አገልግሎት የመጠየቅና የማግኘት
- ➢ ተገልጋዮቹ በጾታ ብሎም ፣ በብሔር በቋንቋ ፣ በዘር ፣ በኃይማኖትና በፖሊቲካ አመለካከት ልዩነት ሣይደረግባቸው በሕገ መንግስቱ መሠረት እኩል አገልግሎት የማግኘት
- ➢ ከተቋሙ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ ፣ ወጪ ቆጣቢና ውጤታማና ፍትሃዊ ያልሆነ አገልግሎት ባጋጠማቸው ጊዜ በየደረጃው ለሚገኙ የቅሬታ ሰሚ አካላት ቅሬታቸውን ለማቅረብና አስፈላጊውን ምላሽ የማግኘት
- ➢ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በጊዜ የማግኘት
- ➢ ስለአገልግሉት አሰጣጥ የሚሰማቸው አስተያየት በነፃነት የመስጠት
- ➢ በተለየ ሁኔታ ትኩረትና አገልግሎት የሚያስፈልጋቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች በልዩ ሁኔታ እገዛና አገልግሎት የማግኘት
- ➢ በዳኝነት ሥራ አካሄድ ጉዳያቸውን በተለየ ምክንያት የሚታይ ካልሆነ በግልጽ ችሎት የመዳኝትና ውሣኔ የማግኘት

### 6. አስተያየት የሚሰጥባቸውና ተሣትፎ የሚደረግባቸውን ሁኔታዎች

- ➢ ፍትህ ለማግኘት ወደ ፍ/ቤት የሚመጡ ተገልጋዮችን ችሎት ከመጀመሩ በፊት ለ30 ደቂቃዎች በማወያየት ሀሣብ አስተያየትና ጥቆማዎችን መቀበል
- ➢ ለተልጋዮች ምቹና ግልጽ በሆነ ቦታ ለአስተያት መስጫ መዝግበውና አስተያየት መስጫ ሣጥን ማስቀመጥ
- ➢ ስለ አገልግሎት አሰጣጥ የሚገልጽ ቅጾችና ከተገልጋይ የሚጠበቅ ቅደመ ሁኔታዎችን ለተገልጋይ መስጠት ፣በግልጽ በሚታይበት ማስቀመጥ / ማቆም/

7. <u>አጠቃላይ የጥራትና የአሰራር መርሆዎች</u>

በዚህ ቻርተር መሠረት የሚሰጡ አገልግሎቶች እስከታችኛው መዋቅራችን ድረስ በተቀመጠው ስታንንደርድ መሠረት ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

8. <u>የቀጠሮ ፖሊሲያችን</u>

የቀጠሮ አሰጣጥ ፖሊሲያችን እስከታችኛው መዋቅራችን የሚሆነው በቀላል በመካከለኛ እና በከባድ ጉዳዮች አንፃር ከሰዓታት እስከ በBPR እስከተወሰነው የመጨረሻ 10 የሥራ ቀናትን የሚያካትት ይሆናል፡፡

9. <u>የአገልግሎት ተደራሽነት</u>

አገልግሎታችን በሥራ ሂደቶችና በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች ባስቀመጥነው ተደራሽ ግቦች መሠረት በተሟላ መልኩ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

10. <u>የአሣታፊነት ሥርዓታችን</u>

በምንሰጠው አገልግሎት በሁሉም መዋቅራችን ተገልጋይ ደንበኞቻችንና የሚመለከታቸውን አካላት በሙሉ በዕቅዳችንና በአፈፃፀማችን በድጋፍና በክትትላችን ወቅትም እናሣትፋለን፡፡

11. <u>ቶሎ ምላሽ መስጠት</u>

ደንበኞቻችን ባስቀመጥነው ስታንደርድ መሠረት ምንም ሣይጉላሉ አገልግሎቱን እንዲያገኙ ጥረት ይደረጋል፡፡

12. <u>ተገልጋይ ተኮር አገልግሎትና የሕዝብ ግንኙነት ሥራን በተመለከተ</u>

የምንሰጣቸው አገልግሎቶች በሕጋዊ አሰራር ውስጥ በተገልጋዩ ፍላጐትና ፈቃድ ላይ የተመሠረቱ እንዲሆኑ ጥረት እናደርጋለን፡፡ የሕዝብ ግንኙነት ሥራዎችን በየወቅቱ በመስራት ለአሠራራችን ግብዓት እናጠናክራለን፡፡

13. <u>ተከታታይነት ያለው መሻሻልና የቻርተሩ ቆይታ ዘመን</u>

13.1 ሥራችንን በየዕቅድ ዘመኑ በመገምገም ክፍተቶችን ለመሙላት ተከታታይነት ያለው ማሻሻያ እናደርጋለን፡፡

13.2 ይህ የዜጐች ቻርተር ለ2007 ዓ.ም ሥራ ላይ ከዋለ በኂላ በዓመቱ በሚገኙ ግብአቶች ሊሻሻል ይችላል፡፡

14. <u>ውጤታማነትን ማምጣት</u>

የፍርድ አሰጣጥ ተልዕኮና ራዕይን መሠረት ያደረጉ ስትራቴጂያዊ ግቦቻችንን ተግባራዊ በማድረግ በጥራት፣በቅልጥፍናና ተደራሽ በሆነ ሚዛናዊ የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡

15. <u>የተሣትፎ ሂደታችን</u>

በሥራችን ሂደትና አፈፃፀም ዙሪያ ከአጋር አካላትና ከሚመለከታቸው ክፍሎች እንዲሁም የሕብረተሰብ የምክክር መድረክ እንዲኖር በማድረግ እና የተለያዩ የመገናኛ ብዙኂንን በመጠቀም እንደአስፈላጊነቱ አገልግሎት አሰጣጣችን እናስገመግማለን፡፡

- ተገልጋዮች ፍ/ቤቶች ስለሚሰጡት አገልግሎቶች ዕውቀት እንዳኖራቸው ማድረግና ያላቸውን አስተያየት እንዲሰጡ ማድረግ

## 16. የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥነ-ሥርዓት

- ተገልጋዩች በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያለባቸውን ቅሬታ የሚያቀርቡት
  - ለፈፃሚው የቅርብ ኃላፊ
  - ለሥራ ሂደቱ ባለቤት / ለም/ፕሬዝዳንት
  - ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ
  - ለፍ/ቤቱ ፕሬዝዳንት

## 17. ክትትልና የግምገማ ሥርዓት

- በቻርተሩ ላይ በተቀመጠው መሠረት ተገልጋዩ አገልግሎት ስለማግኘቱ ፍ/ቤቶች ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ያረጋግጣሉ፡፡
- ስለሆነም ኃላፊነት የለባቸው የሥራ ኃላፊዎች ፣ ሥራ ሂደቶች ወይም አስተባባሪዎች፣ ፈፃሚዎች በቻርተሩ መሠረት ስለመፈጸማቸው በለውጥ ሠራዊት ወይም ድጋፍና ክትትል ኮሚቴ አማካኝነት በየሣምንቱ ፣ በየወሩ በመገምገም ሪፖርት ለተቋሙ ለበላይ አመራር ይቀርባል፡፡
- የበላይ አመራር ኃላፊውም በየወቅቱ የቀረቡትን የክትትልና የግምገማ ሪፖርቶች ላይ በመመስረት የእርምትና የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡
- ተገልጋዮች የየሩብ ዓመቱ ውይይት የሚያደርጉበትና አስተያየት የሚሰጡበት መድረክ ይዘጋጃል፡፡
- የቅሬታ ማስተናገጃ ሥርዓት ተዘርግቶ በየጊዜው ተገልጋዮች የሚሰጡ አስተያየት እየተሰባሰበና እየተተነተነ ማሻሻያ የሚደረግበት አካሄድ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡
- በተደረገው ክትትልና ግምገማ የተገኙ ተጨባጭ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ በቻርተሩ ላይ መደረግ የሚገባቸውን ማሻሻያዎች ካሉ በማናቸውም ጊዜ ማሻሻያ ይደረጋል፡፡
- ተገልጋዮች በተናጥል በሚያደርጉት ክትትል የተገኘ ውጤቶች ተገልጋዮችንና ባለድርሻ አካላት በማሣታፍ በሚደረጉ ውይይቶች ላይ የሚነሱ አስተያቶችን እንደ ግብአት በመቀበል አስፈላጊ የሆኑ ማሻሻያዎች ይደረጋሉ ፣
- ከተገልጋዮች ጋር የሚደረግ የጋራ መድረክ በየ 3 ወር ሆኖ በዚህ መድረክ አጠቃላይ የአፈፃፀም ግምገማ ይደረጋል፡

## 18. የመረጃ አቅርቦትና ስርጭት ሥርዓት

❖ ፍ/ቤታችን የሚያከናቸናቸውን ተግባራት ፣ ዕቅዶች የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶችን እንዲሁም በየወቅቱ የሚያዘጋጃቸውን መረጃዎች እና ሌሎችም የተለያዩ ጽሑፎተና ብሮሸሮች ዘጎች በሚፈልጉበት ወቅት በአካል በመቅረብ ፣ በስልክ እና በሕትመት ውጤቶችን በመጠቀም መረጃውን ሊያገኙ ይችላሉ፡፡በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱ ዘዴዎችን በመጠቀም የሚከተሉትን አድራሻዎች ይጠቀሙ፡፡

| ተ.ቁ | የመ/ቤቱ ስም | ኃላፊነት | አድራሻ | |
|---|---|---|---|---|
| | | | ስልክ | ፋክስ |
| 1 | ሀዋሣ ከተማ ከ/ፍ/ቤት | ኘሬዝደንት ጽ/ቤት | 0916829351 | 0462215125 |
| 2 | ሀዋሣ ከተማ ከ/ፍ/ቤት | ም/ኘሬዝደንት ጽ/ቤት | 0916580151 | |
| 3 | ሀዋሣ ከተማ ከ/ፍ/ቤት | የልማትና ዕቅድ ዝግጅት ጽ/ቤት | 0925632646 | |
| 4 | ሀዋሣ ከተማ ከ/ፍ/ቤት | የሰው ሀብት ባለሙያ ጽ/ቤት | 0911751657 | |
| 5 | ሀዋሣ ከተማ/ የመጀ/ደ/ፍ/ቤት | የመጀ/ደ/ፍ/ቤት ኘሬዝደንት ጽ/ቤት | 0911829162 | 0462211696 |
| 6 | ታበር ምድብ ችሎት | አስተባባሪ ጽ/ቤት | 0468209499 | |
| 7 | ምስራቅ ምድብ ችሎት | አስተባባሪ ጽ/ቤት | 0468209260 | |
| 8 | መሐልና ሐይቅ ዳር ምድብ ችሎት | አስተባባሪ ጽ/ቤት | 0462202996 | |
| 9 | አዲስ ከተማ ምድብ ችሎት | አስተባባሪ ጽ/ቤት | 0462212495 | |
| 10 | ሀዋሳ ቱላየመጀ/ደ/ፍ/ቤት | የመጀ/ደ/ፍ/ቤት ኘሬዝደንት ጽ/ቤት | 0462290252 | |
| 11 | ቱሎና ፍንጭውሃ አካባቢ ም/ችሎት | አስተባባሪ ጽ/ቤት | | |
| 12 | ዳቶና ጨፌ ምድብ ችሎት | አስተባባሪ ጽ/ቤት | | |

## 19. የግብረ-መልስ አሰጣጥ ሥርዓት

ለመ/ቤቱ የሚሰጡ አገልግሎቶችን በተቀመጠው ስታንዳርድ እየተገለገሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ለወደፊት መሻሻል ያለባቸውን ጉዳዮችን በመለየት የአሰራር ሥርዓቱን ቀልጣፋ፣ ተደራሽ ፣ ወጪ ቆጣቢና ወጤታማና ፍትሃዊ በማድረግ ለውጡን ቀጣይነት ያለው እንዲሆን ለዜጎች አስተያየት ግብረ-መልስ መስጠት ወሣኝ በመሆኑ ያላቸውን አስተያየት በአስተያየት መስጫ ሣጥኖች የተዘጋጁ ፎርማቶችን በመጠቀምና በአስተያየት

መስጫ መዝገቦች እንዲሁም በአካል በመቅረብ እንዲሰጡ በአክብሮት ስንጠይቅ በተገኙ ጥቆማዎችና አስተያየቶች ላይ የማሻሻያ እርምጃ ተወስዶ ለባለድርሻ አካላት የሚገለጽ ይሆናል፡፡